



ከዚህ



እስከ፡ዚህ ደረስን ።

በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ

# ከሊቀ ከህናት

## እስከ ፓትሪያርክ



የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ።

www.ethiopianorthodox.org

ቤተ ክርስቲያን እድገት ልክ

ቁጥር 7129

ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
0911860113
0111/271609
D.N Solomon Yohann

# ይ ህ መ ጽ ሐ ት

የተዘጋጀበት ምክንያት ስለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ፱ኛ ዓመት በዓለ ሢመተ ፓትረያርክ ፤

የተዘጋጀበት ክፍል በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትረያርክ የድርሰትና ስነ ጽሑፍ ማዘጋጃ ክፍል

አዘጋጅ ቀሲስ ክንፈ ገብርኤል አልታዩ

www.ethiopianorthodox.org

0911860113
0111271609
D.N Solomon Yohannes

# መ ዓ ር ገ ክ ህ ነ ት

የሥርዓተ ክህነት መዓርግና ክብር በሕገ ልቡና ከአበው ሲያያዝ መጥቶ ከሕገ
ኦሪት ዘመን ሲደርስ ከሌዊ ወገን አሮን ተመርጦ በሥርዓተ ክህነት የእግዚአብሔር የሕጉ
ማደሪያ የሆነችውን ታቦት እንዲያገለግልና ለሕዝቡም ሥርዓትን እንዲሰጥ ተደረገ ፤
በዚሁ ዘመን ሙሴ በምስፍና ተቀምጦ ሕዝቡን ያስተዳድር ነበር ። ሙሴ ለሊቀ ክህ
ናቱ ለአሮን የቤተ ክህነቱን ሥልጣን ሰጥቶት ስለነበር ፤ በቀኙ ተቀምጦ መንፈሳዊ
የሆነውን ነገር ሁሉ ይሰማ ነበር ። ለመጀመሪያ ጊዜ ሳኦል በኋላም ዳዊት ተቀብተው
እስከ ነገሡበት ዘመን ድረስ ሊቃነ ክህናቱ እነኤሊ እነሳሙኤል ከቤተ ክህነቱ አስተ
ዳደር ጋር የመንግሥቱን አቋም ጠብቀው መቈየታቸው ይታወቃል ።

ዘመነ መሳፍንትና ዘመነ ክህናት አልፎ ዘመነ ነገሥታት ከተመሠረተበት ጊዜ
አንሥቶ እነሆ እስከ ዛሬ ድረስ የቤተ ክህነት ባለሥልጣኖች የመንግሥቱ ደጋፊዎች
በመሆን በቀኝ ተሰልፈው በሕግም ሆነ በባህልና በሥርዓት በሃይማኖትም ጭምር
ሕዝቡን ለማስተማር የተለዩበት ጊዜ የለም ። በዚሁ መልክ ኢትዮጵያን ሀገራችንን
ስንመለከት ሥርዓተ ክህነቱና ሥርዓተ መንግሥቱ የተያያዘ ሆኖ እናገኛለን ።

ሥርዓተ ክህነትና ሕገ ኦሪት ወደ ኢትዮጵያ የገቡበት ዘመን የቀዳማዊ ምኒልክ
ዘመነ መንግሥት ሲሆን የአመጣጣቸው ሁኔታ ከዚህ በታች እንደተገለጸው ነው ።

ንግሥት ማክዳ ታምሪን የተባለው ነጋዴዋ ወደ ኢየሩሳሌም ለንግድ ሲመ
ላለስ ከሰሎሞን ጋር ስለሚገናኝ በዓይኑ ያየውንና በጆሮው የሰማውን እየዘረዘረ ያስ
ረዳት ስለነበር የብልሁ የሰሎሞንን ዜና ማየት እንጂ መስማት ብቻ በቂ አለመሆኑን
ተረዳችና ከኢትዮጵያ ወደኢየሩሳሌም ለመሄድ ጉዞዋን ቀጠለች ።

ንጉሥ ሰሎሞንም የመምጣቷን ዜና በሰማ ጊዜ በብዙ ሰልፍና በታላቅ አክ
ብሮት ተቀበላት ፤ ማክዳም ንጉሡ ሰሎሞን ወዳለበት ኢየሩሳሌም ቤተ መንግሥት
ደርሳ ለታቦተ ጽዮን ክብር ገጸ በረከት አቀረበች ። ንጉሡ ሰሎሞንም ንግሥት ማክዳ
ስለሀገሯ ኢትዮጵያ ያላትን መንፈሳዊ ሀሳብ ስለተረዳ የሀገሯን ባህልና የሕዝቡን አም
ልኮት ጠየቃት ። ርሷም በሚገባ ከመለሰችለት በኋላ በፈቃደ እግዚአብሔር የመ
ጣች መሆኗን አወቀ ። ከእርሷም አንድ ምክንያት ማግኘት አለብኝ የሚል ሐሳብ
አደረበት ። በፈቃደ እግዚአብሔርም ከነርሱ ምኒልክ ተወለደ ፤ በበለጠም የሰሎሞ
ንና የንግሥቷ ፍቅር የፀና ሆነ። ምኒልክም የ፳ ዓመት ጐልማሣ በሆነበት ዓመት ወደ
አባቱ ወደሰሎሞን ለመሔድ አሳብ አደረበት ። ከእናቱ ከንግሥት ማክዳ ጠይቆ ስለ
ፈቀደችለት በብዙ ሠራዊት ታጅቦ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደ ። ከአባቱ ከንጉሥ ሰሎሞ
ንም ጋር ተገናኘ ። ሥርዓተ መንግሥቱን በመማር ሦስት ዓመት ከዚያ ሎ ከአባቱ
ዘንድ ከከረመ በኋላ በሰሎሞን ፈቃድ ወደ እናቱ ሀገር ወደኢትዮጵያ በሚመለስበት
ጊዜ ከእሥራኤል ወገን ሕገ ኦሪትን የተማሩ ታሪክ የሚያውቁ ፲፪ሽህ ሕዝቦችና ፳
ክህናት ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ሕገ ኦሪትንና የታሪክ መጻሕፍቶችን በመላ ኢትዮ
ጵያ እየተዘዋወሩ ለኢትዮጵያውያን አስተምረዋል ። የታቦተ ጽዮንም ወደኢትዮጵያ

www.ethiopianorthodox.org

መምጣት በዚሁ ዘመን ስለሆነ ጥንታዊ ታሪኳንና ወደኢትዮጵያ የገባችበትን ለማወቅ ክብረ ነገሥትን እንመልከት ፤ እነዚህም ካህናትና ሕዝቦች ሕግጋት የተጻፉባቸውን መጻሕፍት አብረው ይዘው መጥተዋል ። ሕግጋቱ የቤተ መንግሥቱና የቤተ ክህነቱን መዓርግና መሠረታዊ ሕጋቸውንም የሚገልጹ ናቸው ። ዕከሌቶቹ የሹመት የመዓርጋት ሲሆኑ ደግሞ ዕኩሌቶቹ የስነ ሥርዓትና የሃይማኖት የባህልና የስነ ጽሑፍን ሕጎች የያዙ ናቸው። ለኢትዮጵያ ሕገ ኦሪት ለሕዝቡ እንዲዳረስ በትጋትና በሃይማኖት ሆነው ያስተማሩት ሌዋውያን አባቶቻችን ብዙዎች ቢሆኑም የጥቂቶቹን ስም ከመሳፍንቱና ከካህናቱ በንጉሡ በምኒልክ ፈቃድና ትእዛዝ ሕገ ኦሪትን የሰበኩ እነዚህ ናቸው ።

፩ኛ . አዛርያስ ሊቀ ካህናት ወልደ ሳዶቅ
፪ኛ . ኤልማስ ወልደ አልሚስ
፫ኛ . ናታን ወልደ ነቢይ
፬ኛ . አራም ወልደ ኤስድሮስ መልአከ አሕዛብ
፭ኛ . እስማኤል ወልደ ቦሬስ
፮ኛ . ሰማንያስ ወልደ አኪሳታ
፯ኛ . አድራስ ወልደ አራም
፰ኛ . ሴኬም ወልደ ማትሪም
፱ኛ . አድርዮስ ወልደ ኤስድሮስ
፲ኛ . አዚሳ ወልደ ኩክርዮር
፲፩ኛ. አስተርእዮ ወልደ አስተርኢካ
፲፪ኛ በርንያስ ወልደ አካዝዮል እነዚህ ከካህናቱ ወገን ሲሆኑ ፤ ደግሞ ከመሳፍንቱና ከመኳንንቱ እሚቀጥሉት ናቸው ።

፩ኛ . ቀዳማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት
፪ኛ . ኤልያብ
፫ኛ . አብሔል
፬ኛ . እሜዕ
፭ኛ . ሄት
፮ኛ . ኤዴል
፯ኛ . ጌዴዎን
፰ኛ . ሳዶቅ
፱ኛ . ኤፍሬም
፲ኛ . አብድዩ ናቸው ። ከነዚህም ሌላ ብዙዎች አስተማሪዎች መኖራቸውን ስለቀዳማዊ ምኒልክ የሚተርከው ጥንታዊው ክብረ ነገሥት ያስረዳል ።

ኢትዮጵያ በዚህ ዓይነት ትምህርትና አስተዳደር እየተመራች ከዘመነ ሐዲስ ደርሳለች ።

በዘመነ ሐዲስም ክርስቶስ ያስተማረውን ትምህርት ከሐዋርያው ፊልጶስ ባገኘችው ትምህርት ያለጥርጥር ከኢትዮጵያዊው መኰንን ተቀብላ ስትኖር በመለ ኢትዮ-



ጵያ የክርስቶስ የክቡር ሥጋውና የክቡር ደሙ ሥርዓተ ምሥጢር ወደኋላ ቀርቶ ስለነበ፣ርበአራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ በተነሡት መንፈሳውያን ነገሥታት በአብርሀና አጽብሐ የመንፈስ ኃይልና በብሉዩ መምህር በእንበረም መከከል ጢሮሳዊው ፍሬምናጦስ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንና ማዕርገ ጵጵስናን እንዲያመጣ ተመርጦ ወደ እስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ተላከ ፤ ፍሬምናጦስም የተላከበትን ነገር በዘመኑ ለነበረው ለእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ ለብፁዕ ወቅዱስ አትናቴዎስ አስረድቶ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንም አጥንቶ የጵጵስናን ማዕርግ ተቀብሎ ተመለሰ ። ኢትዮጵያንም በትምህርቱ ብርሀት ስላደረጋት ከሣቴ ብርሃን ሰላማ የሚል ቅጽል ተሰጥቶታል። ከሣቴ ብርሃን ሰላማም በኢትዮጵያ አውራጃዎች እየተመላለሰ የወንጌልን ትምህርት ከመስጠቱም በላይ ከኢትዮጵያውያን መምህራን የተማሩትን እየመረጠ የቅዱስ ወንጌልን ትምህርትና የክርስትናን መስፋፋት ለኢትዮጵያውያን እንዲያስተምሩና በዚሁ መሠረት ቅስና ዲቁና እንዲሾሙ ፤ የኤጲስ ቆጶስነትና የመምህርነት ማዕርግ የተሰጣቸው ኢትዮጵያውያን መምህራን ብዙዎች ቢሆኑም የጥቂቶቹ ስም የሚከተለው ነው ።

፩ኛ . እንበረምን ሕዝበ ቀድስ
፪ኛ . ዓምደ ሃይማኖትን ንቡረ ዕድ ይህም ማዕርግ በዘመኑ ኤጲስ ቆጶስነት ነው ።
፫ኛ . ፓትሪያርክ (በተድባበ ማርያም)
፬ኛ . ርእሰ ርኡሳን (በመርጡለ ማርያም)
፭ኛ . ሊቀ ካህናት (በጣና ቂርቆስ) የተሾሙ ሲሆን ደግሞ በመምህራን በኩል ፤

፩ኛ . ተንሥአ መድኅን
፪ኛ - ተንሥአ ክርስቶስ
፫ኛ . ተጠምቀ መድኅን
፬ኛ . ተጠምቀ ክርስቶስ
፭ . ማዕቀበ እግዚእ
፮ኛ . ተወልደ መድኅን
፯ኛ . ተወልደ ክርስቶስ እያሉ ፤ የማስተማርና የመንፈሳዊ ሥልጣን ሹመት በመስጠት በአጭር ጊዜ ውስጥ በኢትዮጵያ ምእመናን ዘንድ የክርስትና ትምህርት ተስፋፋ ።

ይህም በአቡነ ሰላማ የተመሠረተው የጵጵስና ማዕርግ እንደልማድ ሆኖ በኢትዮጵያ ላይ ከውጪ ሀገር በሚመጡ ጳጳሳት ብዙ ዘመናትን ያሳለፈ በመሆኑ በአንዳንድ መንፈሳውያን ነገሥታትና የቤተ ክርስቲያን አባቶች ቅሬታን መፍጠሩ አልቀረም ነበር ። ስለዚህ አቡነ ተክለ ሃይማኖትንና እጨጌ ፊልጶስን ከነሱም በኋላ በደብረ ሊባኖስ የተሾሙትን እጨጌዎች በማስታወስ የጵጵስናው ፤ የሊቀ ጵጵስናው እንዲሁም የፓትረያርክነቱ ሥልጣን ለኋላ ልጆች መሰጠቱን በጸጋ እግዚአብሔር ሳያውቁት አልቀረም ።ከዚህ ላይ የነቢያትና የሐዋርያትን ምሳሌ መገንዘብ ይጠቅማል ። ነቢያት ሳያዩት ያመኑበትን ክርስቶስን ሐዋርያት አይተው አምነውበታል ።

እንደዚሁም ሁሉ የኢትዮጵያ አባቶች በተስፋ ይጠብቁት የነበረው የጵጵስና ማዕርግ [illegible] ቀደማዊ ኃይለ ሥላሴ የመንፈስ ብርታትና በብፁዕ ወቅዱስ ርእሰ

www.ethiopianorthodox.org

★ ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ ★
0911860113
0111/271609
D.N Solomon Yohannes



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ፤


ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ አቡነ ባስልዮስ አማናዊ ጸሎት ከጵጵስና ወደ ሊቀ ጵጵስና ከሊቀ ጵጵስና ወደ ፓትርያርክነት ደረጃ በመድረሳችን ልዑል እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን ።

ለዚሁም ለከፍተኛው መዓርግ የደረሱትን ሊቃነ ጳጳሳት እግዚአብሔር ለዚህ ለተቀደሰው ተግባር ስለመረጣቸው መላ ኢትዮጵያውያን የአባቶችን የትንቢትና የተስፋ ፍጻሜ ለማየት በቅተዋል ። ይህም ለፍጻሜ በመድረሱ እግዚአብሔር ምን ጊዜም ቢሆን ከኢትዮጵያ ጋር በረድኤት መኖሩን እናምናለን ። ለሀገራችን ይህን ከፍተኛ ዕድል ያስገኘላት ከብዙ አስተብቍዖቷና ጸሎቷ ጋር የተዋሐደው ትዕግሥቷ ነው ፤ ኢትዮጵያ በልዩ ልዩ አምልኮተ ባዕድ—ብሕር የተከበበች ክርስቲያናዊት ደሴት ስትሆን እግዚ አብሔርንም ያወቀችበት ጊዜ ሩቅ ሲሆ



እስከአሁንም ቢሆን ተነፍጓት መኖሩ ይገርማል ። ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ የሃይማኖት የባሕልና የስነ ሥርዓት ሀገር ናት በማለት ብዙዎች ሊቃውንትና ደራስያን መስክረውላታል ። ከቅዱሳንም ወገን ቢሆን በብዛት የሚገኙት የኢትዮጵያ ተወላጆች መናንያን መነኰሳት ናቸው ።

ኢትዮጵያ የብዙዎች ገዳማትና አድባራት ሀገር ስትሆን ጥንታውያን የታሪክ ቅርሶች ይገኙባታል ። ባህሏ የጠበቀ ሥርዓቷ የጸና እምነቷ የበረታ በዓለም ሸንጎ የታወቀች ቅድስት ሀገር መሆኗን ቅዱሳት መጻሕፍትና ታሪክ ይናገሩላታል ። በትዕግሥት ትጠብቀው የነበረው ማዕርገ ጵጵስና በግርማዊ ጃንሆይ፩ኛ ቀዳማዊ ኃይለ



ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ እንደራሴና የሐረር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ፤

ሥላሴ ጥረት ወደ ፓትርያርክነት ደረጃ ከደረሰችበት አንስታ እነሆ በዓመት በዓመት ፓትርያርካዊ በዓል ታከብራለች ። የትዕግሥት መሠረቱ አለመቸኮል ስለሆነ ብዙ ዘመናትን ያሳለፈው መንፈሳዊ ማዕርገ ጵጵስና ሊቀ ጵጵስና የፓትርያርክነትን ማዕርግ ጨምሮ በታላቅ ክብርና ልዕልና ይታያል ። የቤተ ክርስቲያንም መሪዋ ይህ የፓትርያርክነት ስምና ደረጃ ለመሆኑ በየዓመቱ የመታሰቢያውን በዓል ስታስታውሰውና ስታከብረው እግዚ አብሔርን በማመስገንና በጸሎት ነው ።

መሪጌታ መልአኩ ፈለቀ

www.ethiopianorthodox.org

# ከትሕትና ወደ ልዕልና

ይህ ዛሬ የምናከብረው ታላቅ በዓል ከ፩ሺ፺፤ ዓመታት በኋላ የድልና የክብር
ብርሃን የተጐናጸፍንበት ልዩ ጸጋ የወረስንበት ለዘለዓለም የማይረሳ ታላቅ የታሪክ
ዓምድ የተከልንበት በመሆኑ ታሪክና ትውልድ ሲያስታውሰው የሚኖር ነው ።

ቅድስት ድንግል ማርያም እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ያመሰግኑኛል (ሉቃስ
ም፤ ፩፤ ፵፰) እንዳለችው የኢትዮጵያ ሕዝብም ይህን ቀን ሲያመሰግንና ሲያስታው
ሰው ይኖራል ።

የአገርም ሆነ የሕዝብ ታላቅነትና መኖር የሚታወቀው በታሪክ መጽሐፎች ውስጥ
መሥመር ይዞ ሲገኝ ያለፈውንና የራቀውን በቅርብ አድርጎ እንደሚያሳይ ማጉሊያ
መነጽር ጐልቶ ሲታይ በየዘመኑ ለሚፈራረቀው የሰው ልጅ የሚያስረዳ የማይጠፋ
ሠሌዳ በመሆኑ ደስታችን የተነባበረ ነው ።

ይህ ቀን ለክርስቲያኖች ብቻ ሳይሆን ለማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሁሉ አዲስ የታ
ሪክ ጮራ የፈነጠቀበት ዕለት በመሆኑ በታላቅ ደስታ ልናከብረው ይገባናል ፤ አዲስ
ልደት ፤ አዲስ ብርሃን ፤ አዲስ ሥልጣንና የማዕርግ ክብር የተጐናጸፍንበት ቤተ ክርስቲ
ያናችን እንደሌሎች እኩል መንበር የዘረጋችበት ኀዘኗና ጸሎቷ የተሰማበት ቀን
ነው ፤ ሰው በዓለም ላይ ካሉ ፍጡሮች የተሻለ ሆኖ የሚቈጠረውና ሰውነቱ የሚታ
ወቀው ራሱን በራሱ ችሎ የማስተዳደር የመምራት የማስተማር የመንፈሳዊና የሥ
ጋዊ ባለ ሥልጣን ሆኖ ከተገገርነት ቀንበር ወጥቶ የገገርነት መብት ሲረከብ ብቻ
ነው ራሱን እንዳልቻለ ሕፃን ሁል ጊዜ በሞግዚትና እንስሳ ይመስል በመሩት የሚ
ራመድ መሆን የለበትም ቸሩ አምላክ ከቅድስት ማርያም ተወልዶ መከራን የተቀበ
ለና የተሰቀለ የሰውን ልጅ ክብር ለመጠበቅና ከባርነት ቀንበር ነፃ ለማውጣት ስለ
ሆነ የተሰጠንን መብት መልቀቅ የለብንም ።

ይልቁንም የክርስቲያን ደሴት የምትባለው አገራችን እስከዚህ ቀን ድረስ በሞ
ግዚት መቈየቷ የሚያስደንቅ ነው ፤ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የኢትዮጵያ ፓት
ረያርክ ሆነው የተሾሙበትን ቀን ስናከብር ደስታችን በመንፈሳዊ ጸሎት የተሞላ ነው ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እስከ ዛሬ ድረስ በራሷ ልጆች ሳትመራ የቈየ
ችው ሊቃውንት ወይም ለመምራት የበቁ ሰዎች በማጣት አይደለም ። እንዲሁም
ለአምላኳ ስም እንግዳ በመሆን ወይም ጥምቀትን ዘግይታ በመቀበሏ አይደለም ነገር
ግን የፓትረያርክነትን ሥልጣን ሳትጨብጥ የቈየችበት ልዩ ልዩ ምክንያት ስለነበራት
ነው፤ ከምክንያቶቹም ጥቂቶቹ የእስክንድርያውን ፓትረያርክ በጣም ታፈቅርና ታከብር
ስለነበር ያለፈቃድ መገንጠል የሚያስቀይምና የሚያስወግዝ በመሆኑ ከውጭ የሚመጣው
ን ጠላትም በመከራከር ጊዜ በማጣትና የመገናኛ መሥመርም በዚያን ጊዜ ችግር በመሆኑ
እንዲሁም ራስን ከፍ ከፍ ማድረግና ለሥልጣን መሻማትን እግዚአብሔርን እንደማስቀ

www.ethiopianorthodox.org

የም በመቀነጠር ትሕትና ተግባርዋ የሆነችው ኢትዮጵያ በታጋሽነት በኃይል ሳይሆን በስምምነት ጊዜዋን ስትጠባበቅ ቈየች ።

እግዚአብሔር በፈቀደበት ጊዜ በመንፈስ የበለጸጉት በጸሎትና በጾም ፤ በቀኖና በቅንነትና በታዛዥነት አምላክን ያገለገሉት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ለዚህ የመጀመሪያው ዕድለኛ መሪ በመሆን ተመረጡ።ይህም ተጋድሎ የተፈጸመው የግብጽን ፓትሪያርክ በማስቀየም ሳይሆን በእናትና በልጅነት መልክ በስምምነት ጥበብና ትዕግሥት ብልሐትና ቈራጥነት ልዩ ስጦታቸው በሆነው በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ታላቅ ትግልና ድካም ነው ። እንዲያውም ጐን ለጐን ተባብረው እንዲሠሩ በማድረጋቸውም ለቤተ ክርስቲያን ባለውለታ ናቸው ።

ቅዱስነታቸው የምንኵስናን ሕግና ስነ ሥርዓት በደብረ ሊባኖስ ገዳም ጠንቅቀው ያወቁ የምናኔና የብቃትን ክብር በጐሐ ጽዮን በረሃ በዋሻ ሚካኤል ተባሕትዎ ይዘው ጸጋ መንፈስ ቅዱስን ያገኙ ቀኖናንና አገልጋይነትን በጣና ገዳመ ማርያም ያከናወኑ የመንፈሳዊ መሪነትንና አባትነትን በመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል የጀመሩ ታላቅ አባት ናቸው በኢየሩሳሌምም የኢትዮጵያ ገዳም አስተዳዳሪ በመሆን የተወደዱና የተከበሩ ሁነው ቈይተዋል ። ጠላት አገራችንን በወረራት ጊዜ ከግርማዊነታቸው ጋር ማይጨው በቈራጥነት የተሠለፈውን ሠራዊት በማበረታታት እንደታላላቆች ሐዋርያት ተጋድሎን ያለ አንዳች ፍርሀት የፈጸሙ ናቸው ። ታላቁ አትናቴዎስ ከ፪፻፺፰—፫፻፸፫ ዓ/ ም የነበረው ፓትሪያርክ ከሆነ በኋላ ፭ ጊዜ ከመንበሩ በመውረድ ስደትና እሥራትን ለ፲፯ ዓመት ተቀብሏል ። ይኸውም ሲሆን በትዕግሥትና በታማኝነት በመቀበል ከአምላኩና ከቤተ ክርስቲያን ፍቅር አልተለየም ። ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስም ስለሀገራቸውና ስለሃይማኖታቸው ፍቅር ፭ ዓመት በኢየሩሳሌም ተሰደው በነበሩበት ጊዜ እንደ አባታቸው አትናቴዎስ ተስፋ ባለመቍረጥ እንደ ሐዋርያው ጳውሎስ ለጀግናውና ለቈራጡ ሕዝባቸው ከ፲፱፻፴፫—፲፱፻፴፪ ዓ/ም ድረስ ፯ ጊዜ የማጽናኛና የማበረታቻ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል ። በጽሑፋቸውም ውስጥ ለሀገርና ለሃይማኖት መሞት ታላቅ መሥዋዕትነት መሆኑን በማስረዳት ከብሉይና ከሐዲስ በመዘርዘር ለሕዝባቸው በማውገዝና በማዘገዝ አስተላልፈዋል ። ጸሎታቸውንና መልእክታቸውን ምርኩዝና ርዳታ በማድረግ ቈርጦ በመዋጋቱ የክብርና የነፃነት ጌታ ሆነናል ። ነፃነታችን እንደተመለሰም ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ሥራ ፈጽመዋል ።

በጠላት ተቃጥለው ንዋየ ቅድሳት አልባሳትና መጻሕፍት አጥተው የተቸገሩትን አብያተ ክርስቲያናት ከግርማዊነታቸው ከምእመናንም በመጠየቅ እንዲሁም ከግል ንብረታቸው በመስጠት ችግራቸውን አስወግደውላቸዋል ፤ ጠፍቶና ፈርሶ የነበረውን የቤተ ክህነቱን አስተዳደር አቋቁመው ከዘመኑ ጋር እንዲራመድ አድርገዋል ፤ የጥንቱ ትምህርት እንዳይጠፋ በየታላላቁ ገዳም እንዲስፋፋ ዘመናዊ ትምህርት ቤቶችም ከፍተው ችግረኞችን በመርዳት ብዙ ልጆች በነፃ ያስተምራሉ ፤ ካህናቶችና አለቆች በቀለብ እንዲተዳደሩ ፤ በየጠቅላይ ግዛቱም ሊቃነ ጳጳሳትና ጳጳሳት በመሾም የሕዝቡን ችግር አቃለዋል ጽሕፈት ቤትም በየሀገረ ስብ[illegible]



አስተማሪዎችና ካህናቶች በመላክ አብያተ ክርስቲያናትን በማሠራት ስብከት እንዲስፋፋ አድርገዋል ፣ በመንፈሳዊና በሥጋዊ አስተዳደርም የፈጸሟቸው ብዙዎች ስለሆኑ ለመዘርዘር ያዳግታል ።

ከዚህም በላይ የአምላክ ቅን አገልጋይ መሆናቸውን የሚያስረዳው ከ፭ኛው መቶ ዓመት ጀምሮ ቤተ ክርስቲያናችን ራሷን ለማስተዳደር እንድትችል የነበረው ጥረት ሳይሳካ በመቅረቱ እንደገና በይበልጥ በ፲፩ኛው መቶ ዓመት ቤተ መንግሥቱና ቤተ ክህነቱ የክርስቲያኑን ሕዝብ ብዛት በመመልከት ለራስዋ እንድትተዳደር የነበረው ትግል ባለመፈጸሙ ይህን መሠረት በማድረግ በማያቋርጥ ትግል በሳቸው ጊዜ በመፈጸሙና የታሪክ ዓምድ በመሆናቸው ብቃታቸውን የሚመሰክር ነው ።

የአዋጅ ነጋሪ ቃል በምድረ በዳ ይጮሃል የእግዚአብሔርን መንገድ ጥረጉ ጐድጓዳውን አስተካክሉ ዝቅ ያለው ሁሉ ከፍ ይበል ተራራውና ኮረፍታውም ዝቅ ይበል ጠማማውም ይቅና መንገድህን የሚጠርግ መልእክተኛዬን እልካለሁ ። ኢሳ ፵ ፫—፭ ተብሎ በነቢዩ የተነገረው ቃል እውነተኛው ሐዋርያ መንገድ ጠራጊና መሥራች ቅዱስነታቸው በመሆናቸው የመጨረሻውን ዕድል በመቀዳጀታቸው ለፈጣሪ ምስጋና ይገባል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ከእግዚአብሔር የተሰጧቸው ጸጋዎች ብዙዎች ናቸው ። ለድሃ ፍጹም ርኅሩኅና ቸር የተራበ በሬቱ የሚያውቁ ለጋስና ትክክለኛ ተመልካች ማብላትና መመጽወት የሚወዱ ጸሎት ፤ ስግደት ፤ ጾም ፤ ቀኖና እንደ ቅዱሳን አባቶቻቸው የሚያዘወትሩ በቅን ቤተ ክርስቲያንን እንደ አንድ ተራ ሰው የሚያገለግሉ ሥራ ለመምራትና ሠራተኛን ለማሠማራት ልዩ ችሎታ ያላቸው አጣርተውና ደጋግመው ያልተዛነፈ ትእዛዝ የሚሰጡ የሕዝብና የሠራተኛን መብት የሚጠብቁ ሰውን በመፍራት የማይታጠፉ ለሃይማኖታቸው ለሀገራቸውና ለንጉሠ ነገሥታቸው ፍቅር መሥዋዕት የሆኑ ከንቱ ውዳሴ የማይደልላቸው መከራና ሥቃይ የማያጠቃቸው ታጋሽና አስተዋይ ፤ መጽሐፍ መስማትና ማንበብ የሚያፈቅሩ የሚያስስት ስጦታ ያላቸው እንደመናኝ በረሃ ለበረሃና ገዳም ለገዳም የተንከራተቱ በመንፈሳዊ ትምህርት ጥልቅ ዕውቀት ያላቸው የተመረጡና የተወደዱ ፍጹም አባት ናቸው ። ስለዚህ ሕይወታቸውን እንዲጠብቅልን ለኒህ ደግ አባት ጸሎታችንን አናቋርጥም ።

እንዲሁም የቅርብ ረዳታቸውና እንደራሴያቸው ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ታላቁንና ሰፊውን ሥራ በመምራትና በመሸከም ላይ ሲሆኑ የመሸጋገሪያ ዘመን ስለገጠማቸው ያለፈውን ከአሁኑ የሥራ መደብ ጋር ለማሳከትና ለማዛመድ በብዛት የሚጠየቀውን ቤቱ አሻልቶ ስላልያዘ ሰፊ ድካም ጥሎባቸዋል ። ሆኖም ያለመሰልቸት ትዕግሥት ልብሳቸው የሆኑት አባታችን በየአገሩና በየቤተ ክርስቲያኑ በመዘርጋት የኢትዮጵያን ሃይማኖት ለማስፋፋት መንፈሳዊ ማኅበርና ስብከተ ወንጌል ለማቋቋም ስለሚደክሙ እግዚአብሔር ሥራቸውን የተቃና ያደርግላቸው ዘንድ ጸሎታችንን ባለማቋረጥ ለሥራቸውም ተባባሪ መሆን የሃይሃኖታችን ግዳጅ ነው ።

ስሜነህ በቀለ ።

www.ethiopianorthodox.org

# የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓት ረያርክ ጠቅላይ ጽ| ቤት አቅዋም ባጭሩ

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትረያርክ ጠ/ ጽ/ ቤት ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አመራርና አስተዳደር መሪና የበላይ ተቈጣጣሪ ነው ። ስለዚህም በኢትዮ ጵያ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ሥር ላሉት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች የመንበረ ፓት ረያርኩ ጽ/ ቤት ግንዱ ነው ማለት ነው ።

በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥጋዊና መንፈሳዊ አስተዳደር እን ዴት እንደ ሆነ የቤተ ክርስቲያኒቱና የቤተ መንግሥቱ ጥንታዊ ግንኙነትና መረዳዳት እንዴት ተመሥርቶ ሲያያዝ እንደመጣ በተለይም ሲሦ መንግሥት የተባለው ሀብትና ሥልጣን እንዴት እንደተሰጠና አሁንም እንዴት እንደሚሠራበት የመንበረ ፓትረያር ኩን ጠ/ ጽ/ ቤት ጠይቀን የሚከተለውን መግለጫ ሰጥቶናል ።

ኢትዮጵያ በቀዳማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ሕገ ኦሪትን ከተቀበለችበትና በ ሊቀ ካህናቱ በአዛርያስ አማካይነት ታቦተ ጽዮን ወደ ሀገራችን ከገባችበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ዘመነ ክርስትና ማለት አብርሀና አጽብሐ በኢትዮጵያ ነግሠው ያስተዳድሩ እስከ ነበረበት አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ በኦሪቱ እንደ ታዘዘውና እንደተ ሠራው ሕግ ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ ከነገሥታቱ ጀምሮ እስከ ተራው ሕዝብ ለታቦተ ጽዮን መገልገያ ለካህናቱ መተዳደሪያ ለሃይማኖት ማስተማሪያ ቀዳምያት ዓሥራት በኵ ራት እየሰጠ እምነቱን አቈየ ። ይህም ቀዳምያት የተባለው ከሰብሉ ከእሸቱ ከእህሉ ከአ ትክልቱ መጀመሪያ የደረሰውን ማበርከት ሲሆን ዓሥራት ደግሞ ከልዩ ልዩ የገንዘብና የእህል ገቢ ከዓሥሩ አንዱን ዕጅ መስጠት ነው ። በኵራትም የተባለው ከእንስሳቱ ይልቁንም ከልጅ ሳይቀር መጀመሪያ የተወለደውን ለእግዚአብሔር መባዕ መስጠትና ወደ ቤተ እግዚአብሔር ማግባት ነው ።

በዘመነ ሐዲስም ክርስትና በኢትዮጵያ በተሰበከበትና በተስፋፋበት በአብርሀና አጽ ብሐ ዘመነ መንግሥት አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ሊቀ ጳጳስና ሲሾሙና አብያተ ክርስቲ ያናት በየቦታው ሲተከሉ የቀድሞውን ሥርዓተ ኦሪት ሳያፋልሱ ሕዝቡ እንደጥንቱ ቀዳምያቱን ዓሥራቱን በኵራቱን እንዲሰጥ አዘው ስለነበር በዐዋጁ መሠረት አብያተ ክርስቲያናቱ የሚገለገሉት ካህናቱ የሚተዳደሩት መንፈሳዊ ትምህርት የሚስፋፋው ሃይ ማኖት የሚሰበከው ከሕዝቡና ከመንግሥቱ በሚገኘው በዚህ ዓይነቱ ልዩ ልዩ ገቢ ነበረ።

ከነዚህ ሁለት ነገሥታት ጀምሮ በየጊዜው በኢትዮጵያ የነገሡት ነገሥታት መፍቀ ርያነ ሃይማኖት ስለነበሩ በመንግሥታቸው በኩል ከሚሰጡት ሌላ በግል ሀብታቸው ብዙ አብያተ ክርስቲያናት እያሳነፁ ከግል ጒልታቸውና ርስታቸው ቈርሰው መተዳደ ሪያ እየሰጡ አገልጋዮች ካህናትን እየሾሙ ይህን በመሰለ ይዞታ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ይመርዋት ነበር ።



ይህን ዓይነቱን በጎ አድራጎት የሚፈጽሙት ነገሥታቱ ብቻ ሳይሆኑ በየአውራጃው የሚሾሙት ገገርዎች ፤ ሻለቆች ፤ መኳንንት ፤ ሴት ወይዛዝርት ፤ ባላባቶችና የተቻ ላቸውም ምእመናን ሁሉ ነበሩ ።



መምህር ገብረ ሥላሴ ፀሐይ

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትረያርክ ጠ| ጽ| ቤት የአስተዳደር ምክትል ሥራ አስኪያጅ

ከዚያ ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ በአለው አሠራር አንድ አገረ ገገር በአንድ ሀገር ላይ ሲሾም በውስጡ ያሉትን አብያተ ክርስቲያናትና ካህናት ርስት ጉልት፣ሹመት ሽልማት እየሰጠ ማስተዳደር ግዴታው ነበር በዚህም የክርስትና ማዕከለ ዘመን በየ ጊዜው በሚነሡት ደጋግ ነገሥታትና መኳንንት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በሀብ ትም ... ም ሆነ በሠብት እያደገች እስከዚህ ደርሳለች ።

www.ethiopianorthodox.org

ከነገሥታቱም በአምስተኛውና በስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በተነሡት በዓፄ ካሌብና በዓፄ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት ከፍ ያለ የመታወቅና የመደራጀት ዕድል ለቤተ ክርስቲያናችን ተገኝቷል ። በዓፄ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት በታላቁ ሊቅ በቅዱስ ያሬድ የተደረሰው ዜማ እንዲስፋፋ ፤ ለቤተ ክርስቲያናችንም ወደ እግዚአብሔር ምስጋና ማቅረቢያና መገልገያ እንዲሆን ረድቷል ።

ቅዱስ ላሊበላም በንጉሠ ነገሥትነት ሥልጣን የቤተክርስቲያንን መብትና ክብር ከመጠበቁም በላይ ከድንጋይ ፍልፍል ያሰነጻቸው አብያተ ክርስቲያን ነገሥታቱ በስጦታም ሆነ በቤተ ክርስቲያን ሥራ ቀዳሚነት ያላቸው መሆኑን የታሪክ ዓምድ ሆኖ ምስክርነቱን አጽንቶ ይኖራል ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከአዛርያስ ጀምሮ እስከ አቡነ ተክለሃይማኖት ፤ ከቀዳማዊ ምኒልክ እስከ ዓፄ ይኩኖ አምላክ ይህን በመሰለው በነገሥታትና መኳንንት ርዳታና በዓሥራት በኵራት ትተዳደር ነበር ።

ከዚህ በኋላ መንግሥተ ዛጔ ተፈጽሞ ከሰሎሞናዊው ዘር ይኩኖ አምላክ በእግዚአብሔር መሬጭነት በብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቀቢነት ሲነግሥ ለአባቱ ለምኒልክ ዙፋን ላበቃሙና ለመረጠው አምላክ ውለታ ለመመለስና መባዕ ለማቅረብ ያህል ከፍ ያለ በጎ አድራጎት ለቤተ ክርስቲያናችን ፈጽሟል ።

ይኸውም ከቀዳማዊ ምኒልክ እስከ እሱ ዘመን በዓሥራት በኵራት ትተዳደር የነበረችውን ቤተ ክርስቲያን ከሀብቱም ከሥልጣኑም ሲሦውን ሰጥቶ በሀብትና በመብት ማላቁና የመሪዋም መዓርግ ከአዛርያስ እስከ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ዘመን በነበረው የሊቀ ክህናትነት ደረጃ ሳይወሰን ብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን ዕጨጌ በአንት በመሾም ከሊቀ ክህናትነት ወደ ዕጨጌነት ከፍ ማድረጉ ነው ። በኢትዮጵያ በአንት በመሾም — ፌደል ዘር ጀምረው በገ ፊደል ዘር የሚጨርሱ ሦስት ዐበይት የማዕርግ ስሞች አሉ እነዚህም መኳርጋት አፄጌ እቴጌ እጨጌ የሚባሉት ሲሆኑ ለኢትዮጵያ መንፈሳዊና ሥጋዊ አስተዳደር የሥልጣን በሮች ናቸው ።

ዓፄጌ የሚባለው ንጉሠ ነገሥቱ ፤ ዕቴጌ የምትባለው ንግሥቲቱ ሲሆኑ ዕጨጌ የሚባለው የቤተ ክርስቲያኒ መሪ ነው ።

በይኩኖ አምላክ የተሰጠው የቤተ ክርስቲያን ሲሦ መንግሥት አሰጣጡ በገድለ ተክለ ሃይማኖት እንደተጻፈው ይህ ነው ። ይኩኖ አምላክን ቀብተው እንዲያነግሡ ከእግዚአብሔር ታዘ የነገራቸው መልአክ ይኩኖን ቀብተው እንዲያነግሡትና ለሳቸውም ከመንግሥቱ ሲሦውን ሀብትና ሥልጣን እንዲሰጣቸው የእግዚአብሔር ትእዛዝ መሆኑን ሲገልጽ እንዲህ ይላል ።

«ወለከኒ የሀብከ እመንግሥተ ዚአሁ ይኩኖ አምላክ አሐደ ዕደ ወይኩን ለከ ወልደ» ማለት «ይኩኖ አምላክም ከመንግሥቱ ሲሦ አንድ ዕጅ ይስጥህ እሱም ለአንተ ልጅ ይሁንህ» ሲል ያሰጣጡን ትእዛዝ ይጽፍና እልፍ ብሎ ወክልኤሆሙ አጽንዑ ኪዳነ ወመሐላ በደብረ ሊባኖስ ማለት ሁለቱም ተክለ ሃይማኖትና ይኩኖ አምላክ



በደብረ ሊባኖስ የተማማሉትን መሃላና ቃል ኪዳን አጽንተው ኖሩ በማለት አቡነ ተክለ ሃይማኖት በአባትነታቸው መንግሥት ከሰሎሞን ዘር እንዳይወጣ ሊጠብቁ ይኩኖ አምላክም ሢሶ ሀብትና ሥልጣን ከቤተ ክርስቲያን እንዳይነጠቅ እንዲጠብቅ ቃል ኪዳን እንዳደረጉ ይጽፋል ።

ብዕለ ነገሥትም ከዚሁ ተመሳሳይ የሆነ ታሪክ በመተረክና የሢሶ መንግሥቱን አሰጣጥ በማብራራት እንዲህ ሲል ይጽፋል «ውእቱኒ ይኩኖ አምላክ ተካየደ ምስለ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፤ ወወሀበ ሢሶ መንግሥት ወእምይእዜ ይሰመይ ዘመን ዘመነ ኪዳን ይህም ማለት ይኩኖ አምላክ ሢሶ መንግሥትን ሰጣቸውና ከአቡነ ተክለ ሃይማኖት ጋር ቃል ኪዳን አደረገ ፤ ስለዚህ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ያለው ዘመን የቃል ኪዳን ዘመን ይባላል» ይላል ።

ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ የተባለው መጽሐፍ ደግሞ በዘመኑ የነበሩት ጳጳስ አባ ጌርሎስና የሐይቁ መምህር አባ ኢየሱስ ሞዐ ከአቡነ ተክለ ሃይማኖት ጋር እግዚአብሔር ለቀባው ለይኩኖ አምላክ መንግሥትን ለማስመለስ አብረው ጸሎት ወደ እግዚአብሔር እንዳቀረቡና ሀብቱም ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠው በእነዚህ አባቶች አማካይነት እንደሆነ በተከታዩ አሳብ ይገልጣል ለይኩኖ አምላክ ዘሜጠ መንግሥተ እምነ ዛጌ በጸሎተ ጳጳስ አባ ጌርሎስ ወበጸሎተ አባ ኢየሱስ ሞዐ መምህረ ሐይቅ ወበትንብልናሁ ለአብ ብፁዓዊ ክቡር ርእሰ አበው አቡነ ተክለ ሃይማኖት መምህር ዘደብረ ሊባኖስ እስመ ነበሩ በመዋዕሊሁ ኵሎ ኖኀ መንግሥቱ ወበእንተዝ ወሀበሙ አሐደ ዕደ እምሠለስቱ ዕድ መንግሥተ ወምኵናነ ወሥልጣነ ወሢመ እምውሉደ አቡነ ተክለ ሃይማኖት እጨጌ በኪዳን ወመሐላ ወእምውሉደ አባ ኢየሱስ ሞዐ አቃቤ ሰዓት ከመ ይኩን ሎሙ ርስተ ለትውልደ ትውልድ የዚህም ትርጕሙ እግዚአብሔር ለይኩኖ አምላክ መንግሥትን ከዛጔ የመለሰለት በጳጳሱ በአባ ጌርሎስ ጸሎት ፤ በሐይቁ መምህር በአባ ኢየሱስ ሞዐ ልመናና ብፁዕ ክቡር በሚሆን በአባቶች አባት በደብረ ሊባኖሱ መምህር በአቡነ ተክለ ሃይይማኖት አማላጅነት ነው ።

እነሱም በዘመነ መንግሥቱ ነበሩና ከሦስቱም ዕጅ አንዱን ዕጅ መንግሥትን ግዛትን ሥልጣንን ሰጣቸው ፤ ከአቡነ ተክለ ሃይማኖትም ልጆች በቃል ኪዳንና በመሐላ እጨጌነት ሾመ ፤ ከአባ ኢየሱስ ሞዐም ልጆች ዐቃቤ ሰዓትነት ሾመ ይህም ለልጅ ልጅ ርስት እንዲሆናቸው አደረገ ማለት ነው ። እንግዲህ ከዚህ በላይ በታሪክ እንደተገለጠው የዚያን ጊዜው የሢሶ መንግሥት አሰጣጥ ሢሶ ሀብት ብቻ ሳይሆን ሢሶ ሥልጣንም ነው ሢሶ ሀብትም እንኳን ቢሆን የእህል የሌላም ልዩ ልዩ ፍሬ ምድር የቀረጥ የአሞሌ ጨው ነበር እንጂ እንደዛሬው ጥሬ ገንዘብ ብቻ አይመስልም ።

ስለዚህ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከይኩኖ አምላክ ጀምሮ በነገሥታቱና በገዢዎቹ ይህ ሁሉ መብቷና ሀብቷ ተከብሮ በዚሁ ሀብቷ በመላ ኢትዮጵያ ስብከተ

www.ethiopianorthodox.org

ወንጌልን አዳርሶ መምህራንን ሾማ ፤ ሥርዓትን ሠርታ መንፈሳዊ ትምህርቷን እያስ
ፋፋች ኖረች ።

በተለይም በአሥራ አራተኛው ክፍለ ዘመን የነገሡት ዓፄ ዘርዐ ያዕቆብ በንጉሠ
ነገሥት ግዛታቸው የቤተ ክርስቲያንን ሢሶ መንግሥት ከመስጠታቸውም በላይ በክህ
ንነታቸውና በደራሲነት ሞያቸው በዘመናቸው ከነበሩት የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት
ከነአባ ጊዮርጊስ ከነአባ ጽጌ ድንግል ከነአባ ዐርከ ድንግልና ከሌሎችም ታላላቅ
ሊቃውንት ጋር እየተመከከሩ በይበልጥም ለመንግሥታቸው አመራር ረቂቅ ጥበብ
ንና ቅን ፍርድን በሚገልጥላቸው መንፈሰ እግዚአብሔር እየተመሩ ለቤተ ክርስቲያና
ችን የአማረና የተወደደ መንፈሳዊ ሥርዓት ሠሩላት በጣዕመ ቃላቸው የጣፈጡና በም
ሥጢር የተራቀቁ ልዩ ልዩ መንፈሳውያን ድርሳናት ደረሱላት መናፍቃንንና ከሐድ
ያንን እንደ አረም ነቅለው ጣሉላት ። ከዚያም ወዲህ የተነሡት ነገሥታት ለኢትዮ
ጵያ ቤተ ክርስቲያን ብዙ በጎ አድራጎት ፈጽመዋል በጐንደር የነገሠው ዓፄ ኢያሱ
አድያም ሰገድ በዘመኑ ልዩ ልዩ ድርሰቶች ከማስደረሱና ክህናትን በማዕርግ ከፍ ከማ
ድረጉ ሌላ የቤተ ክርስቲያን አበባና ጌጥ የሆነው የአቋቋም ዜማ ይትበሃልና የቅኔ
ስልት መንገድ እንዲይዝና እንዲስፋፋም በዘመኑ ከነበሩት ሊቃውንት ጋር ጥረዋል ።
እነ ዓፄ ዮሐንስ የኢትዮጵያን ሃይማኖት አንድ ለማድረግና አረመኔውን በጥምቀት
ልጅነት እንዲያገኝ የደከሙት ድካም የማይረሣና ቤተ ክርስቲያንም ዓምደ ሃይማኖት
ብላ ልትሰይማቸው የሚገባ ነው ።

ግርማዊ ዳግማዊ ዓፄ ምኒልክም ኢትዮጵያን ዳር እስከ ዳር ሲገዙ በየበላባቱ በየ
ነፍጠኛው በየገገርው ሥር ብዙ ክህናት እየላኩ አብያተ ክርስቲያናት እያሳነፁ ርስት
ጉልት እየሰጡ ሃይማኖትን ማስፋፋታቸው ይታወቃል ። ኢትዮጵያን በሥጋዊው ጥበ
ብም ሆነ በመንፈሳዊው መዓርግ እንድታድግና ወደፊት እንድትራመድ ያደረጉዋት
ደግነትና መንፈሳዊነት ከጥንት አባቶቻቸው ነገሥታት በዘርና በግብር ከደማቸው
የተዋሐዳቸው መፍቀሬ እግዚአብሔር ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት
ዘኢትዮጵያ «ከንተ ያላገኘሁት ምን አለኝ» ብለው የመንግሥታቸውን ዓሥራት ለእግ
ዚአብሔር መባዕ አድርገው በማቅረብ አባታቸው ይኩኖ አምላክ ከአቡነ ተክለ ሃይማ
ኖት ጋር እንደተጋባው ቃል ኪዳን የአቡነ ተክለ ሃይማኖት የመንፈስና የሥራ ልጅ ለሆ
ኑት ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ የኢትዮጵያ ፓትረያርክ በገቡት ቃል መሠረት በበጎ
አድራጎታቸውና በተለመደው ቸርነታቸው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከሰሞን መሬ
ቶች የሚገኘውን ዓሥራትና ግብር የትምህርት ታክስ እንድታገኝ በፈቀዱላት ገንዘብ ነው
አሁን የምትንቀሳቀሰው ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት የተሰጠው ሢሶ መንግሥት ግን አሁን
አለ ለማለት ያስቸግራል ። ምክንያቱም በመሠረተ ግምቱ የምታገኘው ጠቅላላ የዓመት
ገቢ$ 1,82I,142.24 ብቻ ስለሆነ ነው ይኸውም ከዓሥራት $ 1,259,872.93 ሲሆን
ከትምህርት ታክስ ደግሞ $ 561,269 31 ብቻ ነው ። እንግዲህ የቤተ ክርስ
ቲያናችን ገቢ ከአንድ ሚሊዮን ተኩል ብዙ የማይበልጥ ሲሆን የኢትዮጵያ
ቤተ ክርስቲያን ሢሶ መንግሥት አላት ማለት የኢትዮጵያ መንግሥት ገቢ ፫



ሚሊዮን ብቻ ነው ማለት ይሆናል የመንግሥቱ ገቢ ይህ ብቻ አለመሆኑ ፀሓ
ንም ዘንድ በግልጥ ስለሚታወቅ በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሢሶ መን
ግሥት አላት የሚባለው ወሬ እውነት አይደለም ቀድሞ የተሰጠው ሢሶ ሀብት
የትሔደና ነው ዛሬ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ገቢ ይህ ብቻ የሆነው የተባለ እን
ደሆነ ርግጥ ይህ ሢሦ ሀብት በማንኛውም ንጉሥ ዐዋጅ አልተሻረም ።



መምህር ኃሊቡ ታፈሰ

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ| ቤት ዋና ጸሐፊ

እንደቀድሞው አሰጣጥ የኢትዮጵያ መንግሥት ገቢ ከሦስት ተከፍሎ ነበር የተሰ
ጠው ። ይህውም ሢሶ ለነጋሽ ፤ ሢሶ ለአንጋሽ ሢሶ የቀዳሽ ተብሎ ነው የተከፈ
ለው።ሢሶ ለነጋሽ የተባለው ነጋሹ ማለት ንጉሠ ነገሥቱ የሚያገዘበትና የሚጠቀምበት
ነው ። ለአንጋሽ የተባለውም አንጋሹ ሕዝቡ ስለሆነ የሕዝቡ ሀብትና ንብረት ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ሚስ ለቀዳሽ የተባለው ግን ቀዳሺ ቤተ ክርስቲያን ስለሆነች ለቤተክርስቲያን የተሰጠ ነበር ይሁን እንጂ ይህ የቀዳሽ ወይም የቤተ ክርስቲያን ተብሎ የተሰጠው ሀብት በቀን ብዛት ወደአንጋሹ እየተደረበ ሔዷል ።

ለዚህም ምክንያት የሆነው ቀዳሹ ቤተ ክርስቲያንን እያገለገለና እየቀደሰ በልዩ ልዩ ትክል ማለት በእልቅና ፤ በግብዝና ፤ በመሪጌትነት ፤ በሰዓታት በቅዳሴ ይህን ንም በመሳሰለው አገልግሎት ተተክሎ እንዲጠቀምበት በደመወዝ መልክ ከተሰጠው በኋላ እስከዕድሜው ያገለግልና ሲሞት ያንን ቤተ ክርስቲያን የሰጠችውን ርስት ለልጆቹ ያወርሳል ። ልጆቹ ደግሞ በሞያና በክህነት አባታቸውን መስለው ስለማይ ወጡ ለቤተ ክርስቲያኑ ግብር ቶፋ የሚባል ደጅ ጠኒ ይገዙና እነሱ መሬቱን ይዘው ወደ ሌላ ሥራቸው ይሔዳሉ ለቶፋውም እንኳ በቂ ደመወዝ አይሰጡትም ምናል ባት ደኅኙ የሆኑ እንደሆነ በዓመት ከ፲ ብር እስከ ፲፭ ብር ቢሰጡት ነው ። በዚህ ዓይነት ነው ሚስ ለቀዳሽ ተብሎ የተሰጠው ሚስ መንግሥት ወደ አንጋሹ ተደርቦ ሊሔድ የቻለው ።

# ከቤተክህነቱ ሥራ አመራርና ርምጃ በአጭሩ

አቶ ስሜነህ በቀለ የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ም/ ሥራ አስኪያ ጅና የውጭ አገር አብያተ ክርስቲያናት አገናኝ ስለቤተ ክህነቱ የሥራ ርምጃ እንዲ ያብራሩልን ላቀረብንላቸው ጥያቄ የሚከተለውን መልስ ሰጥተውናል ።

ጥየቄ ፤ አቶ ስሜነህ በቀለ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ም/ ሥራ ኡስኪየጅ እንደመ ሆንዎ መጠን የዚህን ሥራ ከተረከቡበት ጊዜ ጀምረው ፍጻሜ ያገኙትና ያላገኙት ሥራዎች ምን ምን እንደሆኑ ቢገልጹልን ?

መልስ ም/ ሥራ አስኪያጅ ከሆኑ ጀምሮ ፍጻሜ ያገኙት ሥራዎች ምን ምን ናቸው ? ተብሎ ለተጠየቅሁት ይህን ጥያቄ ንግግር ባደረግሁባቸው ስብሰባዎችና ቤተ ክርስቲያኖች ውስጥ በየጊዜው ተጠይቄ በሰፊው አስረድቻለሁ ሆኖም ሥራ አስኪ ያጅ ማለት ምን ማለት ነው ? በመጀመሪያ ይህን ላብራራ እወዳለሁ ። አንድ ድርጅት ወይም መሥሪያ ቤት በቦርድ ወይም በበላይ ጠባቂነት የሚተዳደር ሲሆን በዓ መት ተወስኖ በተሰጠው በጀት በራሱ ኃላፊነት ሠራተኞችንም ሆነ ገንዘቡን አገላ ብጦና አዛውሮ ይጠቅማል ብሎ በአመነውና በአቀደው ዓላማ ሠርቶና አሠርቶ እን ቅስቃሴውንም ሆነ ጠቅላላውን አቀዋም መፈጸምና ማስፈጸም የሚችል የዓመት ሪፖርቱን ለበላይ ቦርድ አቅርቦ ጥፋትና ልማቱን የሚያስረዳና የሚጠየቅ በጀቱን ጠብቆ የሚሠራ የሚያስደስት ውጤት ሲያቀርብ ዕድገት ፤ ሲያጠፋ ቅጣትና ከሥራ መወገድ የሚደርስበት ማለት ነው ።

ስለዚህ ፩ኛ በተቻለ መጠን ወጣቶች ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲሳቡ በማግባባ ትና በማስረዳት ፤

፪ኛ በየቤተ ክርስቲያኑ በማስተማር የወጣቶች ማኅበር እንዲቋቋም ከደረገው ምክንያት አንዱ በመሆን ።

፫ኛ በየትምህርት ቤቱ በማስተማር የመንፈሳዊ ማኅበር ተቋቁሞአል ፤ ይልቁንም



ጽ፯ ትምህርት ቤቶች በአንድ ላይ ተጠቃልለው መንፈሳዊ ማኅበር እንዲያቋቁሙ እኔው ራሴ አድርጌ የዚያም ፕሬዝዳንት በመሆን እሠራለሁ ።

፬ኛ ወጣቶች በመንፈሳዊና በሥጋዊ ትምህርት እንዲበለጽጉ ከምናስተምረው ሌላ በብዛት ወደ ውጭ እንዲሔዱ እየተነጋገርንና እያበረታታን ከ፳ በላይ ተማሪ ዎች ወደ ውጪ እንዲሔዱ ከብፁዕ እንደራሴው በማስፈቀድ ልከናል ።

፭ኛ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የበላይ ጠባቂ ለሆኑት ለግርማዊነታቸው የቤተ ክርስቲያንን ድካምና የወደፊት ማሻሻያ ይሆናል ብለን የምናምንበትን ከቻ ርተር ጋር አቅርበን ወደ ቤተ ክህነት አስተዳደር ቦርድ ታዞ በመጠባበቅ ላይ ነን ።

፮ኛ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዲሁም ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና ክቡራን ሚኒስት ሮች በተገኙበት የቤተ ክርስቲያንን አቅዋም ሰፋ አድርገን አስረድተናል ።

፯ኛ ከ፲፰ በላይ በውጪ አገር ፤ ከ፵ በላይ በአገር ውስጥ ልዩ ልዩ ስብሰባዎች ቤተ ክርስቲያናችንን በመወከል እኔው ራሴ እየተከፈልሁ አስተዋውቄአለሁ ፤

፪ ጥያቄ በብዙ ስብሰባዎች ላይ በመገኘት ንግግር ማድረግዎ የታወቀ ሲሆን የአብዛኛው ሕዝብ ቅሬታና ጥያቄ ምንድን ነው ?

መልስ የሕዝቡ ቅሬታና ጥያቄ ብዙ ጊዜ አንድ ዓይነት ነው ፤ አብዛኛው የኢትዮ ጵያ ሕዝብ ለሃይማኖት ፍጹም ቅናትና ፍቅር ያለው በመሆኑ ቤተ ክርስቲያናችን ከዘመኑ ጋር ጐን ለጐን አልተሰለፈችም ሌሎች አጥለቅልቀው ሲያስምጧት ለምን ዝም ትላላችሁ ? አንዳንድ ለሕዝብ የማይስማሙ ባህሎችም መሻሻል አለባቸው የማይለወጥና የማይሻሻል ሃይማኖት ብቻ ነው ባህልና የቤተ ክርስቲያን ስነ ሥር ዓት አቋምና ርምጃዋ አስተዳደርዋ ለምን አይሻሻልም ? ወጣቶች በብዛት ለምን ገብተው አይሠሩም በውጪ አገር ቤተ ክርስቲያን ከማቋቋም የአገራችሁን ውስጥ ችግር ማስወገድ ፤ ተከፋፍሎ በልዩ ልዩ ስም ማኅበር ከማቋቋም በአንድነት ማጠቃለል አይጠ ቅምምን ? ሊቃነ ጳጳሳቱ ለሕዝብ ስለተመረጡ ለሕዝቡ የቅርብ መምህራን መሆን፤ ሲኖ ዶስም በየጊዜው እየተሰበሰበ የሰጠው ውሳኔና የፈጸመው ሥራ ለሕዝብ ተገልጦ በሥራ ላይ መዋል ፤ መንፈሳዊ አባቶች የሕዝቡን ፍላጎት ማርካትና ከወቀሳና ከሐሜት የሚድኑበትን ተግባር እንዲያከናውኑ የዘመኑ ወጣቶች በዘመኑ የሥራ ገበታ መሠ ራጨት አለባቸው ። የካህናት ቍጥር ተወስኖ ደንበኛ ችሎታ ያላቸው በቂ ቀለብ እንዲያገኙ ኮርስም እንዲያደርጉ በየጊዜው ዘመኑ ከፈጠረው የእውቀት ምንጭ እንዲካፈሉ ቢደረግ አልባሳትና ንዋየ ቅድሳት ያጡት እንዲያገኙ የምእመናን ድር ጅት ቢቋቋም በየትምህርት ቤቱ የምግባርና የሃይማኖት አስተማሪዎች ኮርስ ያደ ረጉ መጽሐፍ ተዘጋጅቶላቸው አንድ ዓይነት ትምህርት እንዲያስተምሩ ቢደረግ የግዕዝ ቋንቋ እንዳይጠፋ በየትምህርት ቤቱ እንዲሰጥ ከትምህርት ሚኒስቴር ጋር ተነጋግሮ በሥርዓተ ትምህርት እንዲገባ ቢወሰን በየቦታው የወደቁት መጻሕፍት ተሰብስበው በዘመናዊ ማተሚያ ቤት ቢባዙና ቢተረጐሙ ቅዳሴውና ስብከቱ በምን ሰማው ቋንቋ ጥርት ብሎ ቢነገረን እያለ ይህን የመሳሰለ የሚጠይቀው ብዙ ነው ሆኖም ይህ ሁሉ ሊሻሻል የሚችለው የጠቅላይ ጽሕፈት ቤቱ ጥሩ አቋምና ሙሉ ድርጅት ሲኖረው ብቻ መሆኑን እናምንበታለን ።

[illegible] ቤተ ክህነት ሠራተኞች አንድ ጊዜ ከተቀጠሩበት ደመወዝ ሌላ ጭማሪ እየገኙም ይባላል ፤ ስለዚህ ምን የሚገልጹልን ነገር አለ ? ።

www.ethiopianorthodox.org

መልስ የሰውየው የሥራ ችሎታና ያገልግሎት ዘመኑ ወይም የግል ዶሴው(ማኅደሩ) ሳይ መረመር አልፎ አልፎ በአስተያየት የሚጨመርላቸው አልታጡም፤እንደሌላው መሥሪያ ቤት ግን በዓመትና በ፮ወር ጠቅላላ ጥናት ተደርጎ ጭማሪ የማይደረግበት ምክንያት የሥራው ዕድገትና መሻሻል እንደ መንግሥቱ አቅዋም ኤክስፐርቶችና አስተማሪ ዎች ፤ ችሎታ ያላቸው ሠራተኞችና አማካሪዎች በመቅጠርና በብዛት ገብተው እንዲሠሩ ለማድረግ ባለመቻሉ እንዲሁም ከብፁዓን አበቶች ጋር አብረው በመሰለፍ ተግባብተውና ተመካክረው የሚያገለግሉ በመታጣታቸው የመንግሥቱ መሥሪያ ቤቶች ተወ፡ውረው ሊደርሱ ከሚገባቸው አልፈው በመገኘት የራሳቸውን ወጣቶች በሥራ በማሠልጠንና በከፍተኛ ትምህርት በማስተማር ከውጭ አ ር ዘመዋስ ይገለገሉ የነበሩባቸውን ሰዎች አስወጥተው በመረከብ ለአዲሲቱ ኢትዮጵያ እድገት ሲጣደፉ ማየት ለመንፈስ ደስታን ለሰው ልጅ ኩራትን ሲያተርፍ ቤተክህነቱ ግን እንደመንግሥቱ ኤክስፐር ቶች የውጭ አገር አሠልጣኞች ባይኖሩት በብፁዓን አበቶች መሪነት በነበሩት ሠራ ተኞች በመሰለፍ የሚያደርገው ተጋድሎ የወጣቱን መንፈስ ሊያረካ ባይችልም ሳያስ መሰግነው እንደማይቀር ቢታሰብም በተለይ የአስተዳደር ቦርዱ አባሎች በሥራ ማዕበል የተዋጡ በመሆናቸው ጠለቅ ብለው የሥራውን ዝርዝር ለመመርመር ጊዜ ስለሚያጥራቸውና ከታሰበበት ግብ ባለመድረሱ የገንዘቡ አቅዋምና የሥራው ርምጃ የሠራተኞችም የደመወዝ ጭማሪ ከገቢው ጋር የተዛሠረ በመሆኑ ነው ።

ö / ጥያቄ ፤

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የውጭ አገር አብያተ ክርስቲያናት አገናኝ እንደ መሆንዎም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከውጭ አገር አብያተ ክርስቲያናት ጋር የምታደርገው ግንኙነት እንዴት ነው ? በምንና በምንስ ነው ? ቢያብራሩልን ፤

መልስ ፤

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከውጭ አገር አብያተ ክርስቲያናት ጋር የምታደር ገው ግንኙነት ምንድን ነው ? ተብሎ ለተጠየቀው ፤

ሀ/ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት በሚያደርገው ማንኛውም ጉባኤና ስብሰባ ትገ ኛለች ፤ ስለዚህ መሥራች አባል እንደመሆንዋ መጠን የገንዘብ መዋጮ ታደርጋለች

ለ/ መንግሥት እንደሚያደርገው ሁሉ ቤተ ክርስቲያንም በበኩሉዋ ልዩ ልዩ ድርጅ ትና አመራር ስለአላት የመረዳዳትና የመንፈሳዊ አስተዳደር ውሳኔዎች ስለምታስተላ ልፍ ለሰላምም ሆነ ለሃይማኖት የክርስቲያን አባሎች በሙሉ በአሁኑ ዘመን ተገ ናኝቶ አብሮ ለመሥራትና በጸሎትም ለመቀራረብ ስለሚደረገው ውይይት የኢትዮ ጵያ ቤተ ክርስቲያንም መልእክተኛ በመላክ ትካፈላለች ።

ሐ/ የመንፈሳዊ ተማሪዎችን የቲዎሎጂ (መንፈሳዊ) ትምህርት እንዲማሩ ትልካለች ።

መ/ ልዩ ልዩ አሳብ በመለዋወጥ በዓለም ሰላም እንዲሰፍን ፤ ጦርነት እንዲቀ ርና የሰው ልጅ መብት እንዲጠበቅ በሚደረገው ጉባኤ ተካፋይ ሆና የምትስማ ማበ ትን ወ ሳኔ ታስተላልፋለች ።

ሠ/ በታላላቅ በዓላት ጊዜም የደስታ ምኞት



ክርስቲያኖችና ለበላይ መሪዎች ታስተላልፋለች ።

ረ| የውጭ አገር ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና የድርጅት ወኪሎችን እየጠራች ትጋብዛለች ፤ እንዲሁም ለጉብኝትና ለልዩ ልዩ ሥራ የሚመጡትን በደስታ ተቀብላ ታስተናግዳለች ።

ሰ| ሌሎች እንደሚያደርጉት ሁሉ በውጪ አገሮች ቤተ ክርስቲያኖች በመሥራትና አስተማሪዎች ካህናት በመላክ አስፈላጊውን መንፈሳዊ ተግባር ታከናውናለች

፳| ጥየቄ ፤

በዚህ በኩል የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከዚያየምታገኘው ጥቅም ምን ነገር ይኖራል ?

መልስ ፤

ሀ| በብዛት ተማሪዎች በነፃ እ ሔዱ እንዲማሩ በመለመን እየፈ ዱልን ተ ረው የተመለሱና በመማር ላይም የሚገኙ ብዙዎች ናቸው ።

ለ| ለስብሰባ የሚሔዱትን መልእክተኞች ጠሪው ቤተ ክ ስቲያን ለቲኬትና ለሆ ቴል እንዲከፍላቸው በማድረግ ይጋብዙናል ።

ሐ| ልዩ ልዩ ችሮታዎች ያደርጉልናል ።

መ| ዝዋይ ትምህርት ቤት ሠርተውልናል ።

ሠ| ለ፫ ት|ቤት የሚያገለግል የሳይንስ ላቦራቶር ሙሉ መሣሪያ የራሻ ቤተ ክርስቲ ያን ሰጥታናለች ።

ረ| የካልቸር ልውውጥ ፕሮግራም ተካፋይ እንዲሆኑ የእኛን ተማሪዎች በየዓመቱ በነፃ ያስተምሩልናል ፤ ይህን የመሳሰለ ልዩ ልዩ ርዳታና ችሮታ በየጊዜው ያደርጉ ልናል ።

፳| ጥያቄ ፤ አቶ ስሜነህ ! ብዙዎች ወንዶችና ሴቶች ልጃገረዶች ወጣቶች የእስኮ ላርሺፕ ዕድል እየተሰጣቸው ወደ ውጭ አገር መላካቸው የታወቀ ነው ፤ እነዚህ ወጣቶች ከዚያ ተምረው ሲመለሱ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ምን የሚሰጡት አገ ልግሎት ወይም ጥቅም አለ ።?

መልስ ፤

ወደውጭ እየተላኩ የተመለሱት ለቤተ ክርስቲያን ምን የሰጡት አገልግሎት አለ ? ለተባለው ፤ ከመሔዳቸው በፊት በየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናቸው የእሑድ ትም ህርት ቤት በማቋቋም የቤተ ክርስቲያንን ስነ ሥርዓትና ደግሞ የመጽሐፍ ቅዱስን ትርጉምና ጠቅላላ የሃይማኖት ትምህርት በመማርና በማስተማር ይረዳሉ

፺| ጥያቄ ፤

ወጣቶች ከዚህ ወደ ውጭ አገር ሲላኩ ምንና ምን ያወቁ መሆን አለባቸው ?

መልስ ፤

ወጣቶች ከዚህ አገር ሲሔዱ ምንና ምን ማወቅ አለባቸው ለተባለው ፤ ፫ዓይነት ፕሮግራም አለን ፤ አንደኛው የኮርስ ማለት ነው ፤ በዚሁ ፕሮግራም ተካፋይ የሚ ሆኑት ለአንድ ወይም ለሁለት ዓመታት ብቻ ሲሆን ያላቸውን ዕውቀት እንዲያሻሽሉ አስተማሪዎች በመንፈሳዊ ትምህርት የገፉ ከሆነ በዘመናዊ ትምህርት ...ቱ ይላኩሉ ።

www.ethiopianorthodox.org

ሁለተኛው ለአንድ ዓመት የካልቸርና የአካዳሚክ ልውውጥ ፕሮግራም ተካ ፋዮች የሚሆኑት ናቸው ፤ እነሱም ፤

ሀ/ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የታወቁና በማኅበራቸው የተመረጡ፤

ለ/ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን እምነትና አቋም ጠንቅቀው ያወቁና የኢትዮ ጵያ ኦርቶዶክስ አባል የሆኑ ፤

ሐ/ በዘመናዊው ትምህርት ወንዶች ከ፲፩ኛ ሴቶች ከ፲—፲፩ኛ ክፍል የደረሱ ፤

መ/ ለድርጅቱ መመዝገቢያ ገንዘብ መክፈል የቻሉ ፤

ሠ/ መልክም ጠባይ ያላቸውና ቢያንስ ተሰጥዎ መቀበል የሚችሉ መሆን አለ ባቸው ።

፫ኛው ለከፍተኛ ዲግሪ የሚላኩት ፲፪ኛ ክፍልን የፈጸሙና የመንፈሳዊ ትምህር ትም ያላቸው ናቸው ።

፳/ ጥያቄ ፤

በውጭ አ"ር ያሉት የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ስንት ናቸው ? ለነዚህስ የሚደረገው ወጭ ምን ያህል ነው ?

መልስ ፤

በውጭ አገር ያሉት የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያን ምን ያህል ይሆናሉ ? ለተ ባለው በአሜሪካ ፣ በቶቤጎና በብሪቲሽ ጊያና ፤ በሱዳን በጠቅላላው ፵፫ አብያተ ክር ስቲያናት ይሆናሉ ፤ የእኛን ክህናትና ዲያቆናት ለመላክ የገንዘባችን አቋም ስለአልፈ ቀደልን በውጭ አገር ያሉት የኛ ክህናትም በጣም ትንሾች ስለሆኑ ብዙዎች የአገሩ ተወላጆች እየተማሩ በማገልገል ላይ ይገኛሉ ። ስለገንዘቡ ግን በየጊዜው እንደአስፈ ላጊነቱ ከፍና ዝቅ ስለሚል ይህን ያህል ነው ብለን በበጀት አልወሰነውም ።

፱ ጥያቄ ፤

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለውጭ አገር አብያተ ክርስቲያናት የምትሰጣቸው ጥቅም ምንና ምን ነው ?

መልስ ፤

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለውጭ አገር የምትሰጠው ጥቅም በኅብረትና በመ ረዳዳት ለሚደረገው የመንፈሳዊ ንቅናቄና የአንድነት ትግል በመንፈስና በመተባበር ትካ ፈላለች ። ከዚህም በላይ እንደ አቅሟ የገንዘብ መዋጮ ታደርጋለች ፤ መልእክተኞች ትቀበላለች ፤ ትልካለች ። የስብሰባ ጉባኤ አዘጋጅታ ትጋብዛለች ፤ ለልዩ ልዩ የጋራ ቢሮ ሠራተኞች ቀለብና የቢሮ ኪራይ ታወጣለች ፤ ይህንን በመሳሰለው ትረዳለች ።

፲| ጥየቂ ፤

ከዚህ ሌላ በበኩልዎ ያለዎትን አስተያየት ቢሰጡን መልካም ነው ።

መልስ ፤

አስተያየት እንድሰጥ ከተጠየቅሁ የዘመኑ ትውልድ በመንፈሳዊ ትምህርት ያልበለ ጸገ እንደመሆኑ መጠን ሳይንስና ቴክኖሎጂን የተከተለ ስለሆነ ያ የተመሰገነው የኢ ትዮጵውያን ጀግንነት ፤ ኩሩነት ፤ ትሕትና ፤ እግዚአብሔርን መፍራት ፣ ታማኝነት ፣ ቅን



አገልጋይነት እየጠፋ ከጥንት ቅርሳችን እየተለያየን እንደ ሸቀጥ ተግበስብሶ የገባው ልዩ ልዩ ባህልና ሃይማኖት እኛን በማስጠሙ በየዕለቱ የምንቀስመውን በመውረስ ለአ ገራችን እንግዳ መሆናችንና ሌላ ባህል ማጠራቀማችን የማይጠረጠር ነው ፣ ጠባያች ንም ምን አገባህ ! አ ! አታድርቀኝ ምን ላድርግ አይገባህም በማለት የትሕትናው ጠባይ ወደብልግና ፤ የታማኝነቱ የእጅና የአፍ ውስልትና ፤ ጀግንነቱ ፍርሃትና ዓላማቢስ ፤ እግ ዚአብሔርን ፈሪነቱ የት አለ እግዚኣብሔር ! ወደማለት ፤ የአገር ፍቅር ወደራስ ፍቅር እየተለወጠ ስለሚሔድ የመንፈሳዊ አባቶችና ሕዝቡም መንግሥቱም እያወቁና እየ ሰሙ እንዳልሰማ ችላ ማለት ሳይሆን በአንድ ላይ የስነ ምግባር ዘመቻ ማድረግ ያስ ፈልጋል ። ከሕገ ልቡና ወደሕገ ኦሪት ከዚያም ወደሕገ ወንጌል ከተዛወርንበት ጀምሮ ለኢትዮጵያውያን የአምላካችን ስም እንግዳ የሆነበት የለም ፤ ይልቁንም ሮማውያን ግሪክና ግብፅ በልዩ ልዩ አምልኮ በተዋጡበትና የጣኦት መዲና በነበሩበት ጊዜ ኢት ዮጵያ ከዚህ ነገር ነፃ በመሆኗ ከምስጋና በቀር የወቀሳ መልእክት እንኳ አልተወረ ወረባትም ።

ስለዚህ ይህችን የመሰለች የክርስቲያን እምብርት እንደገና ዛሬ ወንጌል ጠረፍ እስከ ጠረፍ በተሰበከበት ጊዜ ወደኋላ ቀርታ እንደ አዲስ አማኒ የክርስቶስን ምሥራች ሰሚ በመሆኑዋ ለተመልካች የሚያሳዝን ነው ። አለን እያልን አለመኖርም የሚያሳፍር ነው ። ክርስቶስ እኔን ማን ይሉኛል ብሎ ሲጠይቅ ይልቁንም እኛ ሕዝባችንና ሌላው ሰውስ ምን ይሆናል ? በምንስ ይገምተናል ? ሥራችንስ እንዴት ነው ? ብሎ አለመጠየቅና አለማወቅ ሰሚውንና አዋቂውን እንዳልሰማ የሚያስቈጥር ለወራሾቻችን የሚረከቡት እንደማሳጣት የሚቈጠር ነው ። ሕዝቡን ለማገናኘትና ለማስተማር ሃይ ማኖታችንንም ለማጽናት ፤

፩ኛ መንፈሳውያን አባቶች በጭር ታጥቀው ሃይማኖትና በጎ ምግባርን ማስተማር ፤

፪ኛ በየዋሻው የወደቁት መጻሕፍት በየጠቅላይ ግዛቱ እየተመዘገቡ በጠቅላይ ቤተ ክህነት ማተሚያ ቤት እየተባዙና እየተተረጐሙ እንዲቀመጡና ትውልድ ሊያ ነባቸው በሚችል መጠን እየተሻሻሉ ቢወጡ ፤

፫/ ሊቃውንቶች ከማለቃቸው በፊት በቴፕና በጽሑፍ ዕውቀታቸውን ማስቀረት ፣

፬| በጥንቱ ትምህርት የበሰሉ ወጣቶች ሊቃውንት ቢገኙ በቂ ቀለብ እየሰጡ ትምህርት እንዲሰጡ ፤ እነሱም በዘመናዊ ትምህርት ኮርስ እንዲያደርጉ ማድረግ ፤

፭| ክህናት በልዩ ልዩ ኮርስ እንዲሠለጥኑ ማደራጀት ፤

፮| ችሎታ ያላቸውን በቤተ ክህነት በልዩ ልዩ ክፍል ማስገባት ለየሊቃነ ጳጳ ሳቱም ቢያንስ ሁለት በጽሕፈት ቤቱና በየትምህርት ቤቱ እንዲገቡ ማሠራጨት ፤

፯/ የክርስቲያኖች ወጣቶች ንቅናቄና ማኅበር ማቋቋም ፤

፰| የተከፋፈለውን አስተዳደር ወደ አንድ ማጠቃለል ፤

፱| የመንፈሳዊንና የሥጋዊን አስተዳደር ክፍሎ አስተዳደሩ በሚኒስቴር ደረጃ እን [illegible] ጠቅላላ ሃይማኖቶችን ለመቈጣጠርና የእኛም ርምጃ ንዲስፋፋ እን

www.ethiopianorthodox.org

ዲሁም ችግር በገጠመን ጊዜ ወደሚኒስትሮች ምክር ቤት በማቅረብ አስፈላጊውን ማስፈጸምና በኢትዮጵያ ላይ የተዘራውንም ልዩ ልዩ ሃይማኖት በውስጡ አድርጎ መቈጣጠር ይችላል ።

፲| ደንብ አውጥቶ በፓርላማና በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ጸድቆ እንዲፈቀድ ማድረግ ፤

፲፩/ የገንዘብ ማግኛ ምንጭ ማስፋፋት ፤

፲፪| የሕግና የኤኮኖሚ አማካሪ ማቋቋም ፤



አቶ ሰሚነህ በቀለ

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ ጠ/ ቅ/ ቤት ም/ ሥ/ አ
አስኪያጅና የውጭ አገር አብያተ ክርስቲያናት አገናኝ ።

፲፫| በልዩ ልዩ ምክንያት ውጭ የቀረውን ገንዘብ መሰብሰብ ፤

፲፬| አሁን ከሚሠራው በበለጠ ሕዝባችንን በሬዲዮና በታላላቅ ስብሰባ ፕሮግራም አድርጎ ማስተማር ፤

፲፭| ያለንበትንና ለወደፊት የሚገጥመንን ችግር የሚቀጥለውንም ፕሮግራም እያብራሩ ለሕዝብ ማስረዳት ።

፲፮| ሕዝቡ መዋጮ እንዲያደርግ ፕላናችንንና ዓላማችንን ግልጥ አድርጎ ማስተማር ፤

፲፯| ከውጭ አገር ልዩ ልዩ ርዳታና እስኮላርሺፕ መጠየቅ ፤

፲፰| ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ አጥታ ከመዘጋምቱ በፊት ለሥልጣነ ክህነት የሚዘጋጁ ወጣቶች ማፍራት ፤

፲፱| ቀለባቸውንም በየችሎታቸው መደልደል ፤

፳| ዋናውን ጽሕፈት ቤት አጣርቶ በየችሎታቸው የሚደለድል ከውጭና ከቤት




ክህነት ኮሚቴ ማቋቋም ፤

ይህንና ይህን የመሳሰለውን ለቅዱሱ ሕዝባችን በማካፈል በብርሃኑ ንጉሠ ነገሥታችን ጊዜ በንቃትና በትጋት መሥራት ይኖርብናል ። አሁን ረዳታችን ብዙ ነው ፤ ሃይማኖት የሌለው ሕዝብ ከእንስሳ ያልተሻለ ስለሚሆን መነቃቀፍን ፤ መተማማትን ፤ ለሥልጣን መጓጓትን ትተን በደገኛውና በቅዱሱ አባታችን በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባሳልዮስ ጸሎትና ብቃት በግርማዊነታቸው ታላቅ ትግል የጨበጥነውን ከፍተኛ ሥልጣን ዋስትና በማድረግ የእግዚአብሔርን መልእክት ለሕዝባችን ማብሠርና መሥራት የእያንዳንዱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፈንታ እንጂ አንዱ በአንዱ የሚያመካኝበት ጊዜ አይደለም ።

ስለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ጸሎትና ትሩፋት
አቶ ሣህለ ሚካኤል ወልደ ሥላሴ አበርክተውት ከነበረው

## ሥ ወ ድ ስ አ ን ዱ

በነዊኅ ጸሎት ሐፀ ልሳንከ ወበልቡጠ ወርቅ ምጽዋት ወልታ ዕደዊከ ይትዓቀብ
ሃይማኖት ወፍቅር አበግዐ ቤቱ ለላባ
ለያዕቆብ ሕሊና ልብከ አኮኑ ተውህበ



አቶ ሣህለ ሚካኤል ወልደ ሥላሴ

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ
ርክ ቅዱስ ሲኖዶስና የአስተዳደር ጽ/ ቤት ሹም

ወበትረ ሀብትከ ሐመልሚል ያስተባዝኖን ዘልፈ ለአባግዒከ ከመ ዘግባ
ተዐቀኊረሂ ጠለ ከብርከ ለቤተ ክርስቲያን ሕንባባ
እስመ ገድላቲከ ደመናት መልዕልተ ገዳማት (አድባራት) ይረብባ
ዘበኀበ ነህብት ኮንከ ፍቱነ እሳት አባ
ጽሩየ ባሕርይ ወመልክዕ ባስልዮስ ወርቀ ሳባ

## የቤተ ክህነት ንብረት ክፍል

የቤተ ክህነት ንብረት ክፍል ሹም አቶ ጌታሁን ዘውዴ ስለ ንብረት ክፍል እን[illegible] እንደሚከተለው ገልጠውልናል ።

[illegible] የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከጠላት ወረራ በፊት ክርስትና ከጕልት ሌላ

www.ethiopianorthodox.org

ውርስና የዳኝነት ገቢ የማር እሸት የበርና የኬላ የገበያና የሱቅ ቀረጥ የሱቅ አከራይና ተከራይ የባሕር ዛፍ አሹራ ከሌላም ይህንና ይህን ከመሳሰለው ገቢ በላይ ቀለብና ደመወዝ ሌላም ልዩ ልዩ ዓይነት ከመንግሥት የሚሰጥ ችሮታ እንደ ነበራት የተረጋገጠ ነው ፤ ዛሬ ከሕዝቡ የሚሰማው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከሌላው ድርጅት ሁሉ ብዙ ገንዘብ አላት ሀብታም ናት የሚል ሲሆን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ደሀ መስላ የምትታየው እንዴት ነው ?

መልስ በአዲሱ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ከቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ መሬት የሚገኘው ግብሩም አሥራቱም እንደዚሁም የትምህርት ታክሱ ስለ ተፈቀደላት በገቢዋ መጠን ፤ ለካህናት ደመወዝ ለሠራተኞች ለመምህራን ለሥራ ማስኬጃ ለሰባክያን ፤ ይህንና ይህን የመሳሰለውን ወጭ መድበ ከማስተዳደሯም ሌላ ፤ አልባሳት ንዋየ ቅድሳት ለተቸገሩ አብያተ ክርስቲያናት ስጦታ በማድረግ ለአብያተ ክርስቲያናት ማሠሪያ ወይም ማደሻ ርዳታ በመስጠት ትምህርት ቤት በማቋቋምና በመሥራት



አቶ ጌታሁን ዘውዴ

መጋቢ ሀብታት (የቤተ ክህነት ገብረት ክፍል ሹም

ለተቸገሩ ካህናት የገንዘብ ርዳታ በመስጠት ለሀገረ ስብከቱ ሰባክያን በመላክና ስብከተ ወንጌልን በማስፋፋት በውጭ አገር ለተቋቋሙ አብያተ ክርስቲያናት ደመወዝና ሥራ ማስኬጃ በመክፈል ይህንና ይህን ለመሳሰለው የምታደርገው ወጭ ከገቢዋ ጋር ሲመዛዘን እጅግ ብዙ ሆኖ ይገኛል ፤ በዚህም መሠረት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከሰሞን መሬት የምታገኘው ገቢዋ ፤

ሀ| በግብር ፤

ለ| በአሥራት ፤

ሐ| በትምህርት ታክስ ፤

መ| የጤና ታክስ ፤

ሲሆን ከዚሁ የግብር ገቢ በቀጥታ ባለርስቱ ለአገልጋዮች ካህናት የሚሰጠው በመሆኑ ከቤተ ክህነት ግምጃቤት አይገባም እንደዚሁም ከሰሞን መሬት የሚገኘው የጤና ታክስ ገቢ ለቤተ ክርስቲያን ያልተፈቀደ በመሆኑ ሂሣቡን ለማሳየት ያህል እንጂ ከቤተ ክህነት ግምጃ ቤት የሚገባ አይደለም ።

ጥያቄ በጋሻ መሬት ተተክለው ቤተ ክርስቲያንን የሚያገለግሉ ብዙ ካህናትና ገበዞች አሉ እነዚህ ሰዎች እስካሉ ድረስ ብቻ ያገለግሉበታል ? ወይስ ለልጅ ልጅ የሚተላለፍ ርስት ነው ?



መልስ ስለ ቤተ ክርስቲያን አስተዳደር በወጣው ደንብ በ፭ኛው አንቀጽ እንደ ተገለጸው ሁሉ የቤተ ክርስቲያን ርስትና ጉልት ዓይነቱ ብዙ ነው ቤተ ክርስቲያንን ለሚያገለግሉ ካህናት የተሰጠ ሪም ወይም ቀላድ የሚባል ርስት አለ ለአለቆችና ለገበዞች ጉልት የተሰጠ ገባርና መልከኝነት ወይም የቀላድ መሬት አለ መኳንንትና ወይዛዝርት ሌላውም ሕዝብ ሁሉ የገዛ ርስቱን በመንግሥት ፈቃድ እያዛወረ ወደ ቤተ ክርስቲያን ያገባው ርስት አለ ይህንንም የመሰለው ሁሉ በአንድነት ተጠቅልሎ የቤተ ክርስቲያን ርስትና ጉልት ተብሎ ይጠራል ።

ጥያቄ ቤተ ክህነት ከመሬት ግብር ሌላ ሕንፃዎችን ማከራየቷ የታወቀ ነው ፤ ታዲያስ ለሠራተኞች በቂ ቀለብ የማትከፍል ለምንድር ነው ?

መልስ ከሕንፃው ኪራይ የሚገኘውም ገቢ ከሌላው ገቢ ጋር ተደምሮ በበጀት ላይ ውሏል ፤ ለሠራተኞቹም በገቢዋ መጠን ደመወዛቸውን በበጀት ደልድላ ትከፍላለች ።



አቶ ብሥራት ማስረሻ

የብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ ልዩ ጸሐፊ

# የ ቤ ተ ክ ህ ነ ት ፍ ር ድ ቤ ት

ቤተ ክህነት የራሱዋ መንፈሳዊ ፍ ቤት አቋቁማ ስትሠራ የኖረችበት ጊዜው ረጅም ነው መንፈሳዊና ሥጋዊ ዳኝነት ተለይቶ በየረድፉ እንዲሠራ የመጀመሪያው ድንጋጌ የወጣው በታላቁ ቄ ጠንጢኖስ ዘመነ መንግሥት በ፫፻፲፰ ሊቃውንት ውሳኔ ነው ንጉሡ ቄስጠንጢኖስ ሦስት መቶ አሥራ ስምንቱ ሊቃውንት አጥንተው ከሊቀ ጳጳስ እስከ ዐፃዌ ኆኅት (የመጨረሻ አገልጋይ) ያለው በመንፈሳዊ ፤ ከንጉሠ ነገሥት እስከ ኳደሬ (ጭቃሹም) ያለው በሥጋዊ ዳኝነት እንዲታይ ወስነው ያቀረቡለትን አጽንቶ በዚሁ ሲሠራ ኖሮ ነበር የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም ይህኑ መሠረት በማድረግ ስትሠራበት ኖራለች አሁን ግን በአዲሱ ሕግ ቤተ ክህነት የራሱዋን ቤተሰቦች ምእመናን የምትሠራበት የምትቀጣበት ፍጹም መንፈሳዊ የሆነውን ብቻ የምትዳኝበት ዳኝነት አላት በዳኝነቱ የሚያገለግሉትንም መርጣ አቅርባ ንጉሠ

www.ethiopianorthodox.org

ነገሥቱ ይሾምላታል የመንፈሳዊ ዳኝነት ሥራዋን ሳታቋርጥ ትሠራለች ፍጹም መንፈሳዊ የተባለው ዳኝነትም በክህነት በምንኵስና በተክሊል የሕግ ጋብቻና ተመሳሳይነት ባላቸው ዐበይት ጉዳዮች የሚቀርበው ነው በተክሊል በተጋቡ ባልና ሚስት በሚታየው ዳኝነት ባልና ሚስት በቃል ኪዳን ሲጋቡ ባጣ ብታጪ ብመክን ብትመከኚ ሌላም ችግር ቢደርስብን ከሞት በቀር አንለያይም በሚል የዘለዓለም ጋብቻ የሚተማመኑ እሱ እሷን፤ እሱዋ እሱን በመክሰስ በምንም ምክንያት ሊፋቱ የማይገባቸው አንድ አካል ስለሆኑ ይህን የመሰለው ዳኝነት በቤተ ክህነት ፍርድ ቤት የሚታይ ነው የቤተ ክህነቱ መንፈሳዊ ፍ| ቤት ይህን ከፍተኛ ጉዳይ አጥንቶ የራሱን ፍርድ ሊሰጥ ይችላል በጋብቻው መከከል ወንዱን ወይም ሴቷን የሚበድል ከባድ ወንጀል ካለበት ግን ወደሥጋዊ ዳኝነት ይተላለፋል ወንጀል ባልሆነውና በመንፈሳዊው በኩል ግን ተከሰው ወንዱ ወይም ሴቱዋ አልቀርብም የሚል እምቢተኛ ሲገኝ የቤተ ክህነት ፍ| ቤት ከመንግሥት ግንኙነት ያለው ስለሆነ በፖሊስ አስገድዶ ሊያቀርብ ጥፋተኛውንም በእሥር ሊያቈይ ይችላል በመንፈሳዊ ዳኝነት ታይቶ ይግባኝ የሚጠየቅበት ማናቸውም የፍርድ ውጤት ሥጋዊ ነክ የሆነው ወደ ዙፋን ችሎት፤ መንፈሳዊው ግን ለመንበረ ፓትረያርኩ ችሎት ይቀርባል በመንፈሳዊውም ዳኝነት የታየውን ማንኛቸውንም ፍርድ ሥጋዊ ዳኝነት ሊገለብጠው ወይም በራሱ ኀላፊነት ሊሽረው አይችልም» ሲሉ የቤተ ክህነት ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንት ክቡር ፀባቴ ገ| ሥላሴ ወንድም አገኘሁ ገልጸውልናል ።



የይግባኝ ሰሚ ጉባኤ ዳኞች ክቡር ፀባቴ ገብረ ሥላሴ ወንድም አገኘሁ፤መምህር ምትኬ ይመር



መጋቤ ካህናት በየነ ዓሊ የካህናት አስተዳደር ክፍል ሹም

# የቤተ ክህነት ትምሀርት ክፍል

ከቤተ ክህነት የሥራ ክፍሎች አንደኛው የት| ክፍል ነው፤ ቤተክህነት የሀገሪቱን ሕዝብ በማስተማር አገልግሎቷን ስትፈጽም የቈየችበት ዘመን ረጅም መሆኑ የታወቀ ነው መምህራኖቹ ከፊደል አንሥቶ በንባብ በዜማ በቅኔና በመጻሕፍት ትርጓሜ እያስተማሩ ሕዝበ ኢትዮጵያን ሲረዱ ከመንግሥት ወይም ከክፍላቸው ከቤተ ክህነት አብዛኛውን ጊዜ ቀለብ ሥፈሩልን፤ ደመወዝ ቍረጠ[illegible]



ንን ዕጠቁልን ሳይሉ የሚያስተምሩ ከመሆናቸው የተነሣ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ዘመናዊውን የዕውቀት ዕጇታ እስከጨበጡበት ጊዜ ድረስ በሃይማኖት ባህልና በሀገር ትምህርት ቀጥተኛውን ፈር ሳይለቁ መቈየታቸውን ማንም የሚያውቀው ነው ። የሀገራችን ትምህርት በጊዜው ሰዎች ዘንድ ባለመታወቅ ወይም እንዳረጀ አያት በመቍጠር በቀላሉ ይገመት ይሆናል እንጂ የረቀቀ ፍልስፍናና የጠለቀ አስተያየት ያለው ከመሆኑም በላይ ባህልን ሃይማኖትን የታሪክ ቅርስንና ሙሉ በሙሉ የኢትዮጵያዊነት ስሜትን በጥንቃቄ ጠብቆ ያቈየ የሀገሪቱ አደራ አስቀማጭ ነው ይህ ትምህርት ሲሰጥ የኖረው በቤተ ክርስቲያኒቱ አማካይነት ሲሆን በአሁኑም ዘመን ቢሆን ቤተክህነት ይህ አገልግሎት እንዳይቋረጥ ጥረቷ ፍጹም ነው አባቱን የማያውቅ ልጅ አያቱን ሊናፍቅ አይችልም የራሱንና የሀገሩን ትምህርት ሳያጠናቅቅ የሌላውን ብቻ ለማወቅ የሚጥር ሰው የዚሁ ተመሳሳይ ነው በየዘመኑ የሚነሣው ትውልድ ይህን እንዳይረሳው አስተማሪውንና ትምህርቱንም እንዳያጣው የቤተ ክህነት ባለፈው የነበረው ጥረቷ የበረታ ነው የወደፊቱም ምኞቷ የጋለ ነው ጉዳዩ የሚመለከታቸው ሌሎች ክፍሎች ቢጨመሩም የሀገሩ ትምህርትና ዕውቀት ተነፍጎት ወጣቱ ከባህሉ ከቋንቋው ከሃይማኖቱና ከታሪክ ተጠያቂነቱ ቢራቈት በኃላፊነቱ የምትጠየቅበት ስለሆነ ቤተ ክርስቲያን ካሉባት ግዴታዎች አንደኛው ይህ የትምህርቱ ይዞታ መሆኑን አውቃ ባላት አቅምና መብት የትምህርቱ ርምጃ መሥመሩን እንዳይለቅ ለማድረግ ከመጣጣር አልተቆጠበችም የዚህ ዐቢይ ጉዳይ አደራና ኃላፊነት የተሰጠው የቤተ ክህነት የትምህርት ቤቶች ክፍል ነው ።

ይህ ክፍል ከትምህርት ሚኒስቴር ከሕዝባዊ ኑሮ ዕድገትና ከመላው ሕዝብ ጋር ባለው መተባበር የሀገርንና የውጭ አገር ዘመን አመጣሽ ትምህርት በዘመናዊ አቅድ በማስተማር የተቻለውን ሁሉ ይፈጽማል ይህ የትምህርት ክፍል ከፊደል አንሥቶ እስከ ከፍተኛው የሊቅነት ደረጃ በማብቃት የሚረዳ መሆኑ ቢታወቅም መሠረታዊ አቅዋሙ ።

፩ኛ በዐደባባይ ቆመው የሚሰብኩና አስተምረው የሚያጠምቁ ፤ ፪ኛ ቀድሰው የሚያቈርቡ ፤ ፫ኛ በትምህርት ክፍል የሚያስተምሩ መምህራንን ለማስገኘት ነው ። ክፍሉ ይህን ሥራውን ቀጥሎ የተባለውን ዓላማውን በመከተል አያሌ መምህራንን በማፍራት ሲያገለግል ረጅም ጊዜ አሳልፎአል ተግባሩን አሁንም አላቋረጠም ፤

በአሁኑ ጊዜ (ሀ) የሀገርን ትምህርት ጠብቆ ለማቈየት

(ለ) ዘመናዊውንም አጣምሮ ለማስተማር

(ሐ) በመሠረተ ትምህርት ሕዝቡን ለመርዳት ባለው አቅም እየሠራ

፩ኛ በሀገር ትምህርት (በዜማ በቅኔና በመጻሕፍት ትርጓሜ) ብቻ ፲፻፳፩ ት/ ቤቶች

፪ በሀገርና በዘመናዊ ትምህርት ከ፩ኛ እስከ ፲ኛና ፳ኛ ደረጃ ያላቸው ፳ ት/ ቤቶች አሉት ። ከዚህም ሌላ በንባብ በመጠነኛ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት መጀመሪያዎች እንዲሁም ከ፩— ፬ እና ፰ በሚደርሱ ክፍሎች በመሠረተ ትምህርት የሚረዳባቸው በመላው የኢ.ት| ጠ ግዛቶች በየአውራጃውና በየወረዳው በየቀበሌው በየገዳማቱና [illegible] ቍጥራቸው እጅግ የበዛ ጽ/ ቤቶች አሉት ።

www.ethiopianorthodox.org

የትምህርት ክፍሉ ለነዚህ ሁሉ በጠቅላላ ቀጥተኛ ባልሆነና ከቤተ ክርስቲያን በጀት ባልተወሰነ ቀለብ በመተዳደር ከሚያስተምሩት ሌላ ለመምህራንና ለሠራተኞች በዓመት ፩፻ሺ ፯፻፳፭ ብር ለሥራ ማስኬጃ በዓመት ፮፻፳፯ሺህ፯፻፶ ብር ጠቅላላ ድምር ፩ሚሊዮን ፳፯ሺህ፫፻፸፭ ብር ያወጣል ።

አዳሪ ት| ቤቶች የሚገኙት

ሀ| በሸዋ ሰዋስወ ብርሃን

ለ| በሐረር ልዑል ራስ መኰንን

ሐ| በሸዋ ደብረ ሊባኖስ መምህር ገብረ ኢየሱስ

መ| ደብረ ጽጌ ብፁዕ ወቅዱስ ፓትሪያርክ ት| ቤት

ሠ| አ፡ አ ቅድስት ማርያም ት| ቤ ሲሆን የተመላላሽ ት/ ቤቶች በየጠ| ግዛቱ ሁሉ ይገኛሉ ።

በተለይ በአዲስ አ ባ ከተማ ኰልፌ ሰዋስወ ብርሃን ቅዱስ ጳውሎስ ፤ ገፈርሳ ጼዴንያ ማርያም ፤ አቃቂ፤ ቀበና መከነ ሕይወት ገ| መንፈስ ቅዱስ፤ ጕላ ሠፈርና ኪዳነ ምሕረት ራሳቸውን የቻሉ ት| ቤቶች አሉ ። እነዚህ ሁሉ የሀገርንና የውጭ አገርን ቋንቋ ጨምረው የሚሰጡ ዘመናውያን ት| ቤቶች ናቸው ። ከነዚህ ተመሳሳይ በሆኑት በሌሎችም ጠ|ግዛቶች ባሉት ት| ቤቶች መንፈሳዊውና ሥጋዊው ትምህርት በአንድነት ይሰጥባቸዋል ። የቤተ ክህነት የትምህርት ክፍል የሀገር ትምህርት የሚያስተምርባቸው መጻሕፍት፤ ሥርዓተ ትምህርትና የትምህርት ውጤት ማመልከቻ የምስክር ወረቀት (ሠርተፊኬት)የራሱ አሉት፤ሆኖም በዘመናዊው ትምህርት በኩል ሥርዓተ ትምህርት፤ መጻሕፍት መምህራንና ኢንስፔክተርስ ከትምህርት ሚኒስቴር በማግኘት ይጠቀማል ። በመሠረቱም የቤተ ክህነት የትምህርት ክፍል ከትምህርት ሚኒስቴር የጠበቀ ግንኙነት አለው ። ይህ ክፍል ከት ሚኒስቴር የሚጠይቃቸው ርዳታዎች በርከት ያሉ ቢሆኑም የቤተ ክህነቱ የትምህርት ክፍልም የሃይማኖትና የግብረ ገብ የግዕዝና የአማርኛ ሰዋስው መምህራንን የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍትን ለት| ሚኒስቴር ይጠየቃል።

እስከሁን ባለው የሃይማኖትና የግብረ ገብነት ትምህርት ይዘታ ወጣቶቹ የመማሪያ መጻሕፍት ባለማግኘታቸው አሳሮ አልፎ ባስከተለው የስነ ምግባር ድቀትና የሃይማኖት ስሜት ቀዝቃዛነት በቤተ ክርስቲያን ላይ ወቀሳ ይሰማል ። ድቀት አለመባሉ ከዕውነት የራቀ ባይሆንም ቤተ ክህነት የማስተማሪያ መጻሕፍት ተጠይቃ የለችም ያለችበት ጊዜ ባለመኖሩ ከወቀሳ ውጭና ከሐሜቱ ነፃ ናት።የሃይማኖትና የግብረ ገብነት ትምህርት ያለ አንዳች ሁከት እንዲሰጥ የትምህርት ሚኒስቴር የማያስቸግረው ምክንያት ከታወቀና መጻሕፍቱም በካሪኩለሙ ከተመደበ የቤተ ክህነት የት/ ክፍል የማስተማሪያ መጻሕፍት ለመ [illegible] የቤተ ክህነት የትምህርት



ክፍል እስከሁን በመንፈሳዊው ክፍል የራሱን ት| ቤቶች የሚያስተምርባቸው የራሱ መጻሕፍት ናቸው። ለወደፊቱም ከት· ክፍል አልፎ በሰንበት ትምህርት ወጣቶች የሚጠቀሙባቸው ለሕፃናት ፣ ለወጣቶችና ለታላላቆች በሦስት የዕድሜ ደረጃ የተከፈሉ የሃይማኖት መጻሕፍትን አዘጋጅቶ ለማሳተም በመሰናዳት ላይ ነው ። በቅርቡ እንደሚወጣ ይታመናል አሁንም ባለፈው ፶፱ኛ ዓመት የዜማ ምልክቶችንና በቤተ ክርስቲያን ሕዝብ የሚቀበላቸውን የቅዳሴ ሥርዓቶች ( ተሰጥዎ ) አሳትሞ ለሕዝብ አበርክቷል ።

የትምህርት ክፍል እስከሁን በደረገው ርምጃ በሀገር ትምህርት የሠለጠኑ በገዳም መምህርነት

በደብር አለቅነት ፥

በመሪጌትነት ፤

በትምህርት ክፍል በማስተማርና በጽሕፈት ሥራ በማገልገል ራሳቸውን የቻሉ ብዙ መምህራንን አስገኝቷል ።

በቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ ኃላፊነትና በመምህርነት የሚያስቀምጣቸውም በቅኔ ከየመምህራኖቻቸው፤ በዜማ ከቤተ ልሔም በዝማሬ መዋሥዕት ከዙር አምባ፤ በቅዳሴ ከደብረ ዐባይና ከሰለልኩላ የትምህርት ችሎታቸውን የሚያረጋግጥ መተወቂያ ያላቸውና የሊቅነት ደረጃቸው የተረጋገጠላቸውን ነው ። በዚህ ይዞታ የታወቁ ቤተ ክርስቲያን አያሌ ሊቃውንት አሏት ። የሀገራቸውን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ዘመናዊውን ትምህርት ጨምረው ለመምህርነት በመብቃት በቤተ ክህነት የትምህርት ክፍል በሕዝባዊ ኑሮ እድገት ሚኒስቴርና በሌሎችም የመንግሥት መሥሪያ ቤት የሚያገለግሉ ብዙ ናቸው ።

በስመ ክህንና ባደናጋሪነት ለመጠቀም ከሚሞክሩት ልበ ሞኞች በቀር ከቤተ ክርስቲያናችን ሰዎች እምብዛም ያልተማረ አለ ለማለት ባንችልም በቀሳውስት፤ በመነኰሳትና በዲያቆናት በኩል የሚታዩትን ጥቃቅን ስሕተቶች በማረምና በማስተካከል ክህናቶቻችንን ለዘመናዊነት ለማብቃት የትምህርት ክፍል ፩ኛ በአዲስ አበባ በመንበረ ፓትሪያርኩ ግቢ ለመነኰሳት (ሀ) ለቀሳውስትና ለዲያቆናት (ለ) ለቁሰገበዞችና ለሊቃነ ዲያቆናት ሁለት ዓይነት ኮርስ ከፍቶ የቤተ ክርስቲያንን የውስጥ አስተዳደር የምእመናንን አጠባበቅ ትምህርተ አበ ነፍስ የስብከት ዘዴ የዕጅ ጽሕፈት ቍጥር ቋንቋ ጤና ጥበቃና ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን በማስተማር ባለፈው ጊዜ የ፫ ዓመታት ኮርሳቸውን የፈጸሙ መምህራን አሳመርቋል ። አሁንም ሌሎች ክፍሎች በመከታተል ናቸው ። ፪ኛ ኮልፌ በሚገኘው ሰዋስወ ብርሃን መንፈሳዊ ት| ቤት ባደባባይ ቆሞ ለመስበክና አስተምሮ ለማጥመቅ የሚያስችል የቅኔ የብሉይ የሐዲስ ትርጓሜና የዜማ የቅዳሴ ትምህርት ከመስጠቱም በላይ ከ፩ እስከ ፰ተኛ ደረጃ ባለው ዘመናዊ ትምህርት የሚሠለጥኑ ፳፭ ኮርሰኞች አሉት ።

[illegible] ልጠኛ ት| ቤት በሰፊው ለማራመድ በመንበረ ፓትሪያርኩ

www.ethiopianorthodox.org
www.ethiopianorthodox.org

ዳሪ ት/ ቤት ካህናትን በብዛት ማግኘት እንዲችል ብፁዕ ወቅዱስ ፓትርያርኩ አቡነ ባስልዮስ አዘው ሥራው እንዲቀጥል በተስፋ በመጠባበቅ ላይ ነው ። እስከዚያውም በየጠ/ ግዛቶቹ ሁሉ ይህ ዓላማ እንዲስፋፋ የትምህርት ክፍል በመጣር ላይ ነው ። የትምህርት ክፍል ከአሁኑ ይዞታው ወይም ካለፈው ዓላማ ወዲህ በበለጠ ሥራውን ለማስፋፋት የገንዘብ እጥረት ያሠረው መሆኑን ከአንድ ወር በፊት የት| ክፍል ሥራ መሪ አለቃ

ተከታዩን በ፴፯ኛው ገጽ ይመልከቱ

# የታሪክ ድርሰትና ስብከት ክፍል ጽ| ቤት

የታሪክና ድርሰት ክፍል ጽ/ ቤትን በጥብቅነት በሚመሩበት ጊዜ አባ ተፈራ መልሴ ስለክፍሉ እንዲያብራሩልን ጠይቀናቸው የሚከተለውን መልስ ሰጥተውናል

ይህ ጽ/ ቤት ፲፪ ድርጅቶችን የሚመራ ነው ። እነዚህም ድርጅቶች ፤ ታሪክ ፤ ስብከት ፤ የስ፣ከተ ወ፣ጌል ድርጅት ፤ መጽሔት ፤ ጋዜጣ ፤ የወጣቶች ድርጅት ፤ መዝሙር ፤ የእሑድ ት/ ቤት፤ ማስታወቂያ ፤ ሥርዓተ ተክሊል ፤ የቀሳውስት መረጃ ክፍል፤ የስነ ጽሑፍ ምርመራ (ሳንሱር) ክፍል ናቸው ። ፲፪ቱ ክፍሎች እያንዳንዳቸው ራሳቸውን የቻሉ ብዙ ነገሮች የሚፈጸሙባቸው ናቸው ።

ጥያቄ ይህ ጽ ቤት በየአንዳንዱ ክፍል እንዴት አድርጎ ሥራውን እንደሚያካሒድ ቢገልጹልን ?

መልስ ፤ ከላይ እንደተገለጸው ይህ ክፍል ፲፪ ዋና ዋና ክፍሎች ያሉት ሲሆን እያንዳንዱ ክፍል ሥራውን በሚገባ ያከናውናል ። በየክፍሉም የሚከናወነው ጥንታዊ የሆነውን ታሪክ በነዋሪነት በማስቀመጥ እንዲሁም ለዘመኑ ተስማሚ የሆኑትን ልዩ ልዩ ድርሰቶችን በመድረስና በማዘጋጀት የተዘጋጀውንም ድርሰት በጋዜጣ በመጽሔት በፓንፍሌት እያሳተመ ለሕዝብ ያዳርሳል ። ከዚህም ሌላ ቤተ ክርስቲያንንና ምእመናንን በማዋሐድ ወጣቶች በምግባርና በሃይማኖት ጸንተው የቤተ ክርስቲያናቸውን ባህልና ሥርዓት ጠብቀው እንዲኖሩ አባቶች ለልጆቻቸው መልካሙን ቅርስና ባህል ይዘው እንዲያድጉና ከሃይማኖታቸው እንዳይናወጹ የሚያደርጉበትን ምክር የሚሰጥ መገናኛ ድልድይ ሆኖ የሚሠራ ክፍል ነው ።

ጥየቄ በየጠቅላይ ግዛቶቹ ካሉት ሰባክያን ጋር የቤተ ክህነት ታሪክ ድርሰትና ስብከት ክፍል ግንኙነት እንዴት ነው ? ሥራውንስ የሚያካሒደው እንዴት አድርጎ ነው?

መልስ ፤ ግንኙነቱ በጽሑፍና በቃል ሲሆን ከጐንደር ከጐጃምና ከአሥመራ በስተቀር በአሥራ አንዱም ሀገረ ስብከት ቅርንጫፎች መሥሪያ ቤቶች አሉት ። ሰባኪያኑም በየጊዜው የሚፈጽሙትን መንፈሳዊ ተግባር እየላኩ እንዳስፈላጊነቱ በሬዲዮና በጋዜጣ ይገለጣል ። የሚያጠምቋቸው የሐዲሳን አማንያን የስም ዝርዝር በመዝገበ ሃይማኖት ይመዘገባል ።

ጥያቄ ፤ ስንት ሰባክያኖችና ስንት ደራስያን አሉት ? ።

መልስ ፤ በበጀት የሚተዳደሩ ከ፸፻፶ በላይ የሚሆኑ ሰባክያን ሲኖሩ በዋናው መሥሪያ ቤት ፲ ደራስያን ፤ በአዲስ አበባ በየአብያተ ክርስቲያናት ተመድበው እሑድ እሑድ መጓጓዣ እየተከፈላቸው ለምእመናኑና ለወጣቱ ትውልድ የሚያስተምሩ ፳ አስተማሪዎች ይገኛሉ ።

ጥያቄ፤ በጠቅላይ ግዛቱ ያሉ ሰባክያን በወሩ መጨረሻ ደመወዛቸውን ማግኘት ሲገባቸው አያገኙም እየተባለ ይነገራል ። ስለዚህ ክፍሉ ችግሩን ለማቃለል ምን የወሰደው ርምጃ አለ ? ።

መልስ፤ በደመወዝ አከፋፈል በኩል ችግር የሚደርስባቸው የባሌ፤ የገሙ ጐፋ የከፋ ሀገረ ስብከት ሰባክያን ነበሩ ፤ በሌሎቹ አህጉረ ስብከት የሚገኙት ሰባክያን ምንም ችግር የለባቸውም እነዚህም ወደፊት እንዳይቸገሩ የተላኩበት ሀገረ ስብከት ከተገኘው ከማንኛውም ገቢ በየወሩ እንዲከፍላቸው ጥብቅ ትእዛዝ ስለተደረገ ሥራቸውን ያለምንም ቅሬታና ችግር ለመፈጸም ይችላሉ ።

ጥያቄ፤ ለዋናው ቤተ ክህነት የሚሰጠው ጥቅም ምንድነው ? ።

መልስ፤ ይህ ክፍል ለዋናው ጽ፣ቤትም ሆነ ለቤተ ክርስቲያኒቱ የደም ሥር ሆኖ የሚያንቀሳቅስ ክፍል ነው ። የሚሰጠው ጥቅም ይህን ያህል ነው ተብሎ ግምት ሊሰጠው አይችልም ። በጠቅላላው ቤተ ክህነቱን እንደ ዓይን ብሌኔ አድርጎ የሚጠብቅና የሚከባከብ ከመሆኑም በላይ በቤተ ክርስቲያን ላይ ከየትኛውም ክፍል የሚመጣ ጥያቄ ቢኖር ተገቢውን መልስ የሚሰጥ ክፍል ነው ። ይህ ክፍል ማስታወቂያ ክፍል እንደ መሆኑ የቤተ ክርስቲያን አፈ ጉባኤ ሆኖ ማንኛውንም ጉዳይዋን ለሕዝብ የሚገልጥና የሚያሳውቅ ክፍል ነው ።

ጥያቄ፤ በዓመት ውስጥ የሚፈጽማቸው የሥራ ዓይነቶች ብዛት ምን ያህል ይሆናል ?

መልስ፤ በዚህ ክፍል በዓመት ውስጥ የሚፈጸሙት ሥራዎች ብዙ ናቸው ። ለምሳሌ ዘየቀኑ በኢትዮጵያ ሬዲዮ አማካይነት ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ትምህርት በመስጠት እንዲሁም እሑድና በታላላቅ በዓላት በየአብያተ ክርስቲያናቱ ለአባቶችና ለወጣቶች ለሕፃናት ተፈላጊውን ትምህርት በልዩ ልዩ ምሳሌ ከማቅረቡም በላይ በተጨማሪ ከሰኞ እስከ ዓርብ ባሉት ቀኖች በየትምህርት ቤቱ በመዘዋወር ወጣቱን ትውልድ ከቤተ ክርስቲያን ጋራ በማቅረብና በግብረ ገብነት በማነጽ አስፈላጊውን አገልግሎት ይፈጽማል ።

ጥያቄ፤ ይህ ታሪክና ድርስት ክፍል ካለው ይዞታ በይበልጥ ሥራውን ለማሻሻል ምን ዝግጅት ይኖረዋል ? ።

መልስ፤ ክፍሉ እስከአሁንም ቢሆን ብዙ ዝግጅቶችን እያዘጋጀ ማለት ለልደት፤ ለጥምቀት ለትንሣኤ ልዩ ልዩ ትርኢቶችን በወጣቶች ማዕከላዊ ጽ| ቤትና በእሑድ አስተማሪዎች አማካይነት ጠቅላላውን ሕዝበ ክርስቲያን እየጠራ በነፃ በማሳየቱ ይህን ትርኢት የተመለከተ ሁሉ ደስታውንና አድናቆቱን በጽሑፍና በቃል ለታሪክ ድርሰትና ስብከት ክፍል ገልጹዋል ። በዚህ ክፍል የሚከናወነው መንፈሳዊ ተግባር የሚያስደስት በመሆኑ ለየጊዜው ለጠይቆ መረዳት ፕሮግራምና ለዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጣ አዘጋጂዎች የሚጐርፉት ጥያቄዎችና መልእክቶች ብዙዎች ናቸው ። በተለይ [illegible] አዘጋጅ የሚደርሱት ጥያቄዎች በየቀኑ ቢነበቡ እንኳን

www.ethiopianorthodox.org

ሊፈጸሙ አይችሉም ይህም አንድ መሻሻል መሆኑን ያስረዳል ፤ ካለው ይዞታ በይበልጥ ሥራውን ለማሻሻል ምን ዝግጅት አለው ለተባለው እስከዛሬ ድረስ ሥራው የሚከናወነው በዋናው ክፍል ብቻ ሲሆን አሁን ፤ ግን በአዲስ አበባ በሚገኙት አብያተ ክርስቲያናትና በየሀገረ ስብከቱ በአውራጃውና በወረዳም ጭምር ሕዝበ ክርስቲያን የሚተባበሩበት የስብከተ ወንጌል ድርጅት በብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያ ፓትርያርክ እንደራሴ ትጋትና ሃሣብ በመቋቋሙ ወደፊት እያንዳንዱ ድርጅት ከዋናው የስብከተ ወንጌል ድርጅት ጋራ በመተባበር ሥራውን ለማሻሻል ቤተ ክርስቲያንን ከፍ



አባ ገብረ መድኅን ገብረዮሐንስ

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትርያርክ የድርሰት፣የስብከት ክፍልና የእሑድ ት|ቤት የበላይ ኃላፊ

ለማድረግ በመጣደፍ ላይ በመሆኑ ሰፊ የሥራ ፕሮግራምና ዝግጅት በየቦታው ስለሚታይ ለወደፊቱ ማንኛውም ሥራ እያደገ የሚሄድ መሆኑ የታመነ ነው ።

# የትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት

የትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ሥራ አስኪያጅ በነበሩበት ጊዜ አቶ ጌታሁን ዘውዴ ስለማተሚያ ቤቱ አመሠራረትና ጠቅላላ አቋም ተጠይቀው በሰጡት መልስ የትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት በ፲፱፻፴፮ ዓ/ም ተቋቋመ ፤ ይህም ማተሚያ ቤት ቅዱሳት መጻሕፍት እንዲታተሙበት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ማንኛውንም መጻሕፍት በማሳተም እንድትጠቀምበት በማለት የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት አልጋ ወራሽ ልዑል መርዕድ አዝማች አስፋ ወሰን ኃይለ ሥላሴ የማኅተም መኪና ከላይ በተጠቀሰው ዓመ…

www.ethiopianorthodox.org



ዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሰጡ ፤ ይህም በጎ አድራጎት ልዑልነታቸው ምንያህል የቤተ ክርስቲያን ፍቅር እንዳላቸው ያመለክታል ሲሉ ካስረዱ በኋላ ከዚህ በማያያዝ ማተሚያ ቤቱ ከልዑልነታቸው በተሰጠው የማኅተም መኪና ሥራውን ቀጥሎ በደረገው ርምጃ ዘመናዊ አውቶማቲክ መኪናዎችን ከውጭ ሀገር በማስመጣት ከፍ ያለ ግሥጋሤ አድርጓል ። ማተሚያ ቤቱም ከተቋቋመ ጀምሮ ፯ የሚሆኑ ሥራ አስኪያጆች በየጊዜው ሲሾሙበት ፯ተኛው ራሳቸው እንደሆኑ ገለጹ አሁን ግን ፰ኛው ሥራ



አለቃ ዓምደ ጽዮን ተሰማ

የአሁኑ የትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ሥራ አስኪያጅ

አስኪያጅ አለቃ ዓምደ ጽዮን ተሰማ ናቸው ። ከዚህም በኋላ አሁን በማተሚያ ቤቱ ስንት ሠራተኞች እንዳሉና ለቤተ ክህነትም ስለሰጠው ጥቅም ተጠይቀው መልስ ሲሰጡ አሁን በማተሚያ ቤቱ በለቀማ ክፍል፤ በመኪና ክፍል ፤ በጥራዝ ክፍል ፤ በጽሕፈት ቤትና በልዩ ልዩ የሥራ ክፍሎች ተመድበው የሚያገለግሉ ፸፰ ሠራተኞች፤ ሲኖሩት ማተሚያ ቤቱ እንደሌሎች ማተሚያ ቤቶች ሁሉ ሠርቶ በሚያገኘው ገቢ ይተዳደራል ለቤተ ክህነት ስብከተ ወንጌል አገልግሎት የሚውሉትን አስፈላጊዎች መጻሕፍትን በማደራጀት ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውሉትን መጻሕፍትን በየሳምንቱ የሚወጣውን ዜና ቤተ ክርስቲያን የተሰኘውን ጋዜጣ በማተም የጽሕፈት መሣሪያዎችን ማለት ልዩ ልዩ መዛግብቶችን ክርኔዎችን በጠቅላላው ለሀገረ ስብከቱ ሁሉ አስፈላጊ የሆኑትን እያዘጋጀ ሲያቀርብ የሠራበትንም ሂሣብ ለቤተ ክህነት በየጊዜው ያስታውቃል ፤ ስለዚህ ይህ ማተሚያ ቤት ይህን የመሰለ አገልግሎት በመስጠት ቤተ ክርስቲያንን ያገለግላታል ብለን እናምናለን ሲሉ አስረዱ ፤ ከዚያም ስለማተሚያ ቤቱ የወደፊት መሻሻል ጉዳይ ሲያስረዱ ለጊዜው አሁን ማተሚያ ቤቱ ያለበት ቤት ጠባብ ከመሆኑም በላይ በቂ መጋዘን አለመኖሩን እንደዚሁም በመሣሪያ በኩልም ምንም እንኳ አሁን ያሉት ዘመናውያን መሣሪያዎች ቢሆኑም እንደ ሥራው መጠን ብዙ ተፈላጊ መሣሪያዎች እንደሚያስፈልጉ ገልጸው በዚሁ ዓመት ከሚያስፈልጉን መሣሪያዎች አንዱ የሆነውን አፍሴት የተባለ እን… የኢትዮጵያ ፓትርያርክ እንደራሴ ፈቅደውልን ስለገ

ህን ሥራውን በመሥራት ላይ ይገኛል ሥራው በ፲፱፻፶፰ ዓ|ም ተቋቁሞ ከፍ ያለ የሥራ ፍሬ አስገኝቷል ፣ ወደፊትም የዚሁ ሥራ እየተስፋፋ እንደሚሔድ በሰፊው የታሰበበት ነው ሲሉ መግለጫቸውን አበቁ ።



የሊቃውንት ጉባኤ አባሎች

# ቤተ መጻሕፍት

በመንበረ ፓትርያርኩ ግቤ አንድ ቤተ መጻሕፍት በቅርብ ጊዜ ተቋቁሞአል ። ይህ ቤተ መጻሕፍት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ መልካም ፈቃድና ትእዛዝ በ፲፱፻፶፫ ዓ. ም. ተቋቋመ ። ቤተ መጽሐፉ የተቋቋበት ጊዜ ቅርብ እንደመሆኑ መጠን የተሟላ ድርጅት የለውም ። ለጊዜው ከ፯፻ በላይ የሚሆኑ ልዩ ልዩ ጥንታውያን መጻሕፍት ተሰብስበዋል ። ከነዚህም ውስጥ ፶ የሚሆኑት የብራናና የ እጅ ጽመፍ ናቸው




መሪጌታ መልአኩ ፈለቀ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ፓትሪያርክ የቤተ መጻሕፍት ኃላፊ ።

የቀሩት ግን በማኅተም የታተሙ ናቻ ው ። ዘመኑም ከ፩፻ አይበልጥም ፣ እነዚ መጻሕፍት የተጻፉት በግዕዝ ፤ በአማርኛ ፤ በዐረብኛ ፣ በእንግሊዘኛና በብራይስጥ ቋንቋዎች ነው ።



የቤተ መጽሐፉ ኃላፊመሪጌታ መልአኩ ፈለቀ ባሁኑ ጊዜ ቤተ መጽሐፉን ስለገጠመው ችግር ሲናገሩ ጥንታውያን የሆኑ የብራና መጻሕፍትን ከየገዳማቱና ከየአድባራቱ እያስመጣን ሁለት የቁም ጸሐፍት ቀጥረን በማስገልበጥ የመጻሕፍቱን ቍጥር ለማብዛት ጀምረን ነበር ፣ ነገር ግን እነዚህ ጸሐፍት ከነባጀታቸው ወደ ሌላ ክፍል ስለ ተዛወሩ የተጀመረው ሥራ ለጊዜው ቆሟል ብለዋል ።

በስነ ጽሑፍ ሀብቱዋ በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ የታወቀችው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ወደፊት መጻሕፍትን ሁሉ በሚገባ ማቅረብና መሰብሰብ ፣ ክብሩዋ ነው ብዙ መጻሕፍት ያላት መሆኑን እናምንበታለን ። በየዋሻውና በየገዳማቱ የአይጥና የብል መፈንጫ ሆነው የቀሩት መጻሕፍት ሁሉ ቢሰበሰቡ ለሀገራችን በቂዎች ቅርሶች ሁነው ተከታዩን ትውልድ ያስተምራሉ ። የውጭ አገር መንገደኞች አገር ለመጐብኘት በመጡ ቍጥር መጻሕፍቶቻችንን ለላንቲካ ሲሉ እየገዙ እንዳይወስዱአቸው ጥብቅ ቍጥጥር ማድረጉ አስፈላጊ ነው ብለዋል ።



አቶ የማነ ወ|አማኑኤል በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጠ|ቅ መንበረ ፓትሪያርክ ቤት የመዝገብ ሹም

ከ፴፱ኛው ገጽ የዞረ

ዓምደ ጽዮን ተሰማ ገልጸዋል ።

ከቤተ ክህነት ትምህርታቸውን እየፈጸሙ የሚወጡት ደቀመዛሙርት በተማሩት ትምህርት በይበልጥ ሊያገለግሉ የሚችሉት በስብከት በትምህርት ክፍል በማስተማርና በቤተ ክርስቲያን አስተዳደሪነትና የውስጥ አገልግሎት ሲሆን ሙያቸው በማናቸውም የሥራ ሜዳ የማያሳፍራቸው እንዳጨው ከሁል ገብ ቅመሞች ናቸው ። ሆኖም እስከዛሬ በሀገር ትምህርት ለሠለጠኑት መምህራን የሚቈረጥላቸውን ደመወዝ አጥጋቢ ካለመሆኑ የተነሣ ጥቅም በመፈለግ ወደሌላ ሥራ እየተወራጩ እንዳይባክኑ ቤተ ክህነት በሚቻላት ሁሉ የሊቃውንቱዋን መተዳደሪያ ማሻሻል ያለባት መሆኑ አይሠወርም ። ባለቤቱ ያቀለለውን አሞሌ ባለዕዳ አይቀበለውም እንደሚባለው ራስዋ አክብራ ያላስተዳደረቻቸውን የሀገር ቋንቋ የታሪክ የባህል ተጠያቂነት ያላቸውን ሊቃውንቶቿን ሌላውም ደረጃቸውን ዝቅ አድርጎ ሊገምትባቸው ይሞክራል ። አሁንም ተሞክሮ ታይቶዋል ተሰምቶዋልም ።

የቤተ ክህነት የትምህርት ክፍል በበጀት በኩል አሁን ካለው የተሻለ ጥረት

www.ethiopianorthodox.org

ከገና የወደፊት የሥራ ይዞታውን በበለጠ ለማራመድ ዕቅድ ያለውና ለዚህ ሁ
ችግር መፍትሔ ለማስገኘት የሚያስችል መሆኑን አለቃ ዓምደ ጽዮን ተሰማና ዋ
ጸሐፊው ቄስ ኃይሉ ደክር አሳባቸውን ገልጸዋል ።

# መጋቤ ሐተታ (መቈጣጠሪያ ክፍል)

የቤተ ክህነት መቈጣጠሪያ ክፍል ሹም አቶ አሰፋ መኮሪያ ከስብከት ክፍ
ለቀረበላቸው ጥያቄ መልሱን ቀጥሎ ያቀርባሉ ።

፩ኛ የመቈጣጠሪያ ክፍል የተቋቋመው ከ፴፰ ዓ. ም ጀምሮ መሆኑን እየገለጸ
የተቋቋመበትም ተግባር የጠፋውንም ሆነ የለማውን የቤተ ክርስቲያን ሀብትና መብ
ለመቈጣጠር ነው ።

በዚሁ መሠረት ተቈጣጣሪ ሠራተኞቹ በየጠቅላይ ግዛቶችና በየአውራጃዎ
ተሠማርተው ባደረጉት ምርመራ በብዙ ሺህ የሚቈጠር የገንዘብ ጉድለት እያወጠ
ብዙው በፍርድ ተወስኖ ከማስፈጸሚያው መሥሪያ ቤት ደርሶ ይገኛል ።

፪ኛ ተቈጣጣሪነቱ ከጠቅላይ ጽሕፈት ቤቱ እስከ ጠቅላይ ግዛቶች ላለው ንብረ
ሁሉ ነው ። የሚቈጣጠረው ከዋናው መሥሪያ ቤት እየታዘዘ ከመሆኑ በስተቀር እን
ገንዘብ ሚኒስቴር እንስፔክሲዮን ክፍል ራሱ አስተናብሮ ለመሥራት መብት አልተ
ጠውም ።

፫ኛ የሚቈጣጠረው ገንዘብ ብቻ ሳይሆን የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ንብ
ቶችን እንዲሁም የሥራ አረማመድና አፈጻጸምን ጭምር ነው ።

፬ኛ/ ክርስት የሚገኘውን የግብርና የአሥራት የትምህርት ታክስ ገቢ መንግሥ
በወሰነው መሠረት ግምት ዓይነት የቤት ኪራይንና ማናቸውንም ልዩ ገቢ ለያንዳንዱ
በተወሰነው ታሪፍ ልክ ይቈጣጠራል ።

፭ኛ፡ የመቈጣጠሪያ ክፍል መብትና ኃላፊነት ፩ኛ ቀደም ብሎ እንደተገለፀወ
ከጠቅላይ ግዛቶች እስከ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽሕፈት ቤት ባሉት ቀርንጫፎች መሥሪ
ቤቶች ውስጥ የሚሰበሰበውን የገቢና የሚሠራበትን የወጭ ሂሣብ መመርመርና የሥ
ራውንም ሁኔታ በምን አኳኋን ላይ እንዳለ ለማወቅ ሠራተኛ ልክ መከታተል ፪ኛ ለ
መገዝም ሆነ ለሥራ ማስኬጃ ከተወሰነው በጀት በላይ ገንዘብ እንዳይወጣ መጠበ
ነው መቈጣጠሪያ ክፍል የሀብትና የሥራ መብት ጠባቂ እንደመሆኑ መጠን በገንዘ
ሚኒስቴር እንስፔክሲዮን ዓይነት በቤቱ አቅም ልክ ድርጅት እንዲኖረውና ራሱን ችሎ
እያስተናበረ እንዲሠራ ማድረግ ፤ ድርጅቱም ፩ኛ በሥራው ልክ ሠራተኛ እንዲኖረወ
፪ኛ ጠቅላላ የሀብት ምንጭ የሆነው የመሠረተ ግምትና የታሪፍ ዝርዝር እንዲሰጠው
፫ኛ የክፍሉ ሹም ሠራተኞቹን በራሱ አዛዥነት በየጠቅላይ ግዛቱ እያሠማ
ሂሣብ ማስመርመርና መከታተል እንዲችል ፬ኛ ለሠራተኞቹ የተዘጋጀ የቀን አበ
ተወስኖለት እንዲቀመጥ መደረግ ነበረበት ።

፮ኛ፡ በገዳማትና አድባራት ያለውን ሂሣብ ለመቈጣጠር የሚከለክል ነገር የለም
ነበር ። ይሁን እንጂ በካህናቱ በኩል ያለው አሠራር የታመነ ሂሣብ ለማስገኘት አይ



ችልም ። የሚሠሩት እንዳስፈለጋቸው ዓይነት ከመሆኑም በላይ ገቢውም በታሪፍ የተ
ጨበጠና በመዝገብ የታወቀ አይደለም ። የሚገኘውም ከሥዕለትና ከያንዳንድ የዕለት
ትሮታ ነው ፤ የተጨበጠ ገቢ ያላቸው የዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ቤትና የመንበረ
ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ደብር የደብረ ሊባኖስ ገዳም ናቸው ። የሌሎቹ ግን ገቢያቸው
የመሬት ግብር ብቻ ሆኖ እሱውም የደብር አለቆችና ካህናት ራሳቸው እየተቀበሉ
የሚተዳደሩበት ነው ። በዚህም ላይ ከቤተ ክህነት የሂሣብ መምሪያና ሞዴልነት ያላ
ቸው መዛግብት አልተሰጧቸውም ። ስለዚህ ይህንን ያህል ገቢና ወጭ አለ ለማ
ለት አላስደፈረም ።

# በመጋቤ ሀብታት ሥር ያሉ ክፍሎች

## ነገረ ፈጅ ክፍል

የቤተ ክህነት ነገረ ፈጅ ክፍል ሥራና ዓላማ ምን እንደሆነ እንዲያስረዱን የክ
ፍሉን ጥብቅ ዋና ነገረ ፈጅ አቶ አፈወርቅ ወ/ ኪሮስን ጠይቀናቸው የሚከተለውን
መልስ ሰጥተውናል ።

፩ ጥያቄ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ነገረ ፈጅ ክፍል መብቱ
ከምን እስከምን ድረስ ነው ?

መልስ በክርክር ደረጃ የሆነ እንደሆነ ከአጥቢያ ዳኛ እስከ ጠቅላይ ፍርድ
ቤት በአስተዳደርም በማንኛውም ክፍል ሲሆን በጠቅላላው እስከ ዙፋን ችሎት ለማ
ድረስ መብት አለው ።

ጥያቄ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ነገረ ፈጅ ክፍል በገንዘብ ነክ
ብቻ ነው? ወይስ በሃይማኖት በኩል የሚደርሰውን ሁሉ ይቋቋማል ?

መልስ ይህ ክፍል ለጊዜው የተሰጠው መብት ለአብያተ ክርስቲያናት ርስትና
ገንዘብ ቤተ ክህነት በምትከሰውና በምትከሰስበት ንብረትና ሀብት በሚደርሰን ማስረጃ
የምንከራከርና የምንከላከል ነን እንጂ ከዚህ ሌላ መምሪያ አልተሰጠንም ።

ጥያቄ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አምልኮትና እምነት በጽሑፍ ሆነ በቃል
ለሚሰነዘረው ዘለፋ ያገባዋል?ወይስ አያገባውም ?

መልስ ይህ በቀጥታ ነገረ ፈጅን የሚመለከት ሆኖ አይታይም ዳሩ ግን በሕግ
እንደተጻፈው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን አምልኮትና እምነት በግልጽ
በመንቀፍ ተሳድቦ ወደ ፍርድ ሸንጎ ለማቅረብ ከሚያበቃ ማስረጃ ጋራ ሲደርሰን
ክርክሩን ለፈጠረው ምክንያት ወይም ነገር የተደነገገውን ሕግ ጠቅሶ መክሰስና ስለ
ቅጣቱም የተጻፈው አንቀጽ እንዲፈጸምበት ለማድረግ ይቻላል ።

ጥያቄ መከላከል የሚገባው ከሆነ እስከሁን ድረስ ለተጻፉት የዘለፋ ጽሑፎች
ተከራክሮ ምን ያስገኘው ውጤት አለ ?

www.ethiopianorthodox.org

መልስ የጽሑፍ ዓይነቱ ብዙ ነው ምክንያቱም በጽሑፍ የሚገለጹ ነቀፌታዎችን ለመቋቋም በሊቃውንት እየተዘጋጀ በጽሑፍ መልስ የሚሰጠው በድርሰትም ማስተባበያ የሚደረግባቸው እንጂ በ፫ኛው ተራ ከገለጽነው በቀር ነገረ ፈጅን አይመለከትም

ጥያቄ ይህ ነገረ ፈጅ ክፍል በወር ሆነ በዓመት ከልዩ ልዩ ክፍሎች ተከራክሮ የሚያስገኘው ገቢ ምን ያህል ይሆናል ?

መልስ የዚህ ዓይነቱ የገቢ ግምት በዕለትና በዓመት የሚወሰን ወይም እንደመሬት ሰብልና እንደሌላው የገቢ ምንጭ ዓይነት የሚታይ ሳይሆን ነገረ ፈጅ በጠቅላላው አስተያየቱና ግምቱ እንደ ጦር ወታደር ምሳሌ ነው ። ምክንያቱም ቤተ ክህነት በተከሰሰ ጊዜ ተከላክሎ መልስ የሚሰጥ የራሱም የቤቱ ሀብት ሲወሰድበት ተከላክሎ ለማዳንና ለማስመለስ ሲሆን ንብረቱ ካልተወሰደና ቤቱም ካልተከሰሰ መጠባበቅ ነው ። ሆኖም ነገቶ ያለክርክር ተውሎ አያውቅም ስለዚህ እንደሌላው የገቢ ሁኔታ በ፡ቀኑ ይህን ያህል ተወሰነ ለማለት ቢያዳግትም አብዛኛው ጊዜ በክርክር ይሰነብታል አልፎ አልፎም ብዙ ጉዳይ ያስወስናል ። በ፶፰ ዓ፡ ም $265.270.74 የሚያወጣ ንብረት ተፈርዶልናል ።

ጥያቄ ይህ የነገረ ፈጅ ክፍል ከውጭ ተከራክሮ ከሚያስገኘው ጥቅምና በቤቱ ላይ ከሚያስከትለው ኪሣራ ማንኛው ያመዝን ይመስልዎታል ?

መልስ የሚያስገኘው ጥቅም በይበልጥ ያመዝናል ።

ጥያቄ በ፶፱ ዓ፡ ም ስንት ፋይሎች ተከፍተው ተገቢ ውሳኔ ያገኙትንና ያላገኙትን ዘርዝረው ቢገልጹልን ?

መልስ የ፶፱ ዓ፡ ም የክርክር ብዛት ፩፻፶፰ የንብረቱ ሂሣብ ግምት $ 1.444 846.14 አብዛኛው ለውሳኔ ከተቀጠረው በቀር በፍርድ የተወሰኑ ብዛት ፴፩ ፤ የተፈረደልን ገንዘብ ሂሣብ $40 856.04 በአስፈጻሚዎች ተከታታይነት የገባ $16269.80 ይሆናል ።

ጥያቄ ስለሥራችሁ አፈጻጸም ረገድ በቤቱ በኩል የምታገኙት ርዳታና የሚገጥማችሁ ችግር እንዳለ ቢገልጹልን ?

መልስ ችግሩ ከፍ ያለ ነው ይኸውም ከገንዘብ ሚኒስቴር የአገር ውስጥ ገቢ በኢንካም (ገቢ) ታክስና በኢክስሳይዝ ቀረጥ ማዘጋጃ ቤትም እንዲሁ በከተማ ክልል ውስጥ በሚገኝ የቤተ ክርስቲያን ክልል ቦታዎች የቤተ ክርስቲያን ንብረት ከሆኑ ቤቶች የአከራይ ተከራይ በመቶ ሁለት ቀረጥ ሌላም ይህንን በመሳሰለው ግብር ከጥቅሙ ሁሉ ቀረጥ እንዲከፈልባቸው በየጊዜው ለራሳቸው በነጋሪት ጋዜጣ እያሳወጁ በዚህ ዐዋጅ መሠረት ቤተ ክህነት እንዳትከፍሉ ስለሚሉ በአውራጃና በከፍተኛ በጠቅላይ ፍ/ ቤትም በርከት ባለ ክርክር ላይ እንገኛለን፡፡ነገር ግን ስለ ቤተ ክርስቲያን ንብረትና ሀብት በ፴፭ ዓ፡ ም የተሰጣት ሕግ ፪ ዓመት ቍጥር ፫ ድንጋጌ ብቻ ስለሆነ የማዘጋጃ ቤትና የአገር ውስጥ ገቢ በየጊዜው ለሚያወጧቸው ሕጎች ማፍረሻ ካል መጣ ይህ




የተጠቀሰው ሕግ ከመክፈል አያድንም የማለት አስተሳሰብ በመኖሩ ቤተ ክህነት በተፈቀደላት መሠረት የሕግ ረቂቅ እያቀረቡ ስለመብቷ በነጋሪት ጋዜጣ እንዲወጣ ማድረግ የሚሻል መሆኑን በመደጋገም ጠይቀናል ። ፪ኛም የየአንዳንዱ ክፍል የደብር አለቆች በአላባው እንዲተዳደሩበት የተሰጠውን የቤተ ክርስቲያን መተዳደሪያ የአለቆች ማደሪያ መሬት አልፎ አልፎ የቀድሞዎቹ አለቆች እንደግል ርስታቸው ሸጠው ለውጠው በመገኘቱ አሁን በያዙት ሰዎች ላይ ክስ ሲቀርብ የይርጋው ጊዜ እየደገፈ መከራከሪያ መንገድ በመታጣቱ ቤተ ክርስቲያን ተነቅላ እንዳትቀር ለዚህ የሚደግፍ ትእዛዝ ወይም ሕግ ማስወጣት የሚያሻ መሆኑንም የተደጋገመ ሀሳብ አቅርበናል ።

ለወደፊቱ ጭቅጭቅ እንዳይፈጥርና ክርክርም ቢያጋጥም ማስረጃው የተሟላ ሆኖ ለማግኘት ይቻል ዘንድ ማናቸውም የአብያተ ክርስቲያናት ንብረት የሆነ ሁሉ በደንብ እየተመዘገበና እየተጠና ማስረጃ የሌለው ማስረጃው እየተሟላ በጥንቃቄ እንዲያዝ አሳስበን ለመፈጸሙ የሚሰጠውን መልስ በመጠባበቅ ላይ ነን ።

www.ethiopianorthodox.org

# የርስት ክፍል

ስለቤተ ክህነት ርስት ክፍል የርስት ክፍሉ ሹም የሆኑትን አቶ በትረ ገብረ መድኅንን ጠይቀናቸው የሚከተለውን ማብራሪያ ሰጥተውናል ።



አቶ በትረ ገብረ መድኅን
የርስት ክፍል ሹም

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ስንት ርስት ? አላት ለተባለው በየሀገረ ስብከቱ አልፎ አልፎ በክርክርና በልዩ ልዩ ምክንያት ያልተገመቱ መሬቶች አይታጡም ፤ ሆኖም ለጊዜው በዚሁ ዘመን የታወቀው የአሥራ አንዱ ሀገረ ስብከት የ፵፱ ዓ ም ግምት

ተከታዩን በ፺፬ኛው ገጽ ይመልከቱ

## የሂሳብ ቤት

የጠቅላይ ቤተ ክህነት ሂሳብ ሹም የሆኑት አቶ ተሾመ ዓለማየሁ ስለ ሂሣብ ክፍሉ ሥራ ርምጃ ጠይቀናቸው የሚከተለውን መግለጫ ሰጥተውናል ።


ጥ ያ ቄ ፩ኛ| አቶ ተሾመ ፤ ከግብርና ከቤት ኪራይ እንደዚሁም ከልዩ ልዩ ገቢ በዓመት በዓመት ምን ያህል የተጣራ ገቢ እንደ ተደረገ ቢገልጹልን ?

መልስ በገቢ በኩል ፥

| | |
|---|---|
| ሀ\| ከአሥራት | $1. 259. 872. 93 |
| ለ\| ከትምህርት ታክስ | $ 561, 269. 31 |
| ሐ\| ከቤት ኪራይ | $ 348. 288- 55 |
| መ\| ከልዩ ልዩ ገቢ | $ 121. 737. 43 |
| ድምር ፤ | $ 2. 291. 168. 22 |



በፊደል ሁለት ሚሊዮን ሁለት መቶ ዘጠና አንድ ሺህ አንድ መቶ ስድሳ ስምንት ብር ከሃያ ሁለት ሣንቲም ከአዲስ አበባና ከየሀገረ ስብከቱ በ፲፱፻፵፰ ዓ፣ ም መጨረሻ ላይ በተገኘው ሒሣብ መግለጫ ማረጋገጥ ተችሏል ።



አቶ ተሾመ ዓለማየሁ
በኢትዮጵያ ቤት ክርስቲያን ጠቅ ላይ ቤ|ክህነት ጽ|ቤት የሂሣብ ሹም

ጥ ያ ቄ እንደ ገቢው ለአዲስ አበባና ለሀገረ ስብከቱ ደመወዝና ሥራ ማስኬጃ የተፈቀደውን የወጭ በጀት ሒሣብ ምን ያህል እንደሆነ ቢያስረዱን ?

ተከታዩን በ፺፫ኛው ገጽ ይመልከቱ

# በመጋቤ ካህናት ሥር ያለ ክፍል


## የሠራተኞች ማስተዳደሪያ

የሠራተኛ ማስተዳደሪያ ክፍል ለማንኛውም መሥሪያ ቤት የሠራተኛ ማስተዳደሪያ ክፍል ያለው ሥልጣን አለው ። በቤተ ክህነት ሥር ለሚመሩት ድርጅቶችና ቅርንጫፎች መሥሪያ ቤቶች ሁሉ በተሰጠው ሥልጣንና መምሪያ መሠረት ተገቢ የሆኑትን ሠራተኞች እየመረጠ ይቀጥራል ። ከተቀጠሩም በኋላ ሥራቸውን በትጋትና በቅልጥፍና እንዲያከናውኑ መቈጣጠር ተግባሩ ነው ። በአሁኑ ጊዜ ከ፯፻ በላይ የሚሆኑ የቢሮ ሠራተኞች በየሀገረ ስብከቱ ጽሕፈት ቤት ተቀጥረው እንደሚሠሩና ከነዚህም ውስጥ ፩፻፹ የሚሆኑት በዋናው ጽሕፈት ቤት እንደሚገኙ የሠራተኛ ማስተዳደሪያ ጥብቅ ሹም አቶ ደምሴ ጸጋዬ ገልጠዋል ።

እነዚህን ጽሕፈት ቤት ያላቸው አህጉረ ስብከቶች በሚገባ ለመምራት በቂ ትምህርትና የሥራ ችሎታ ያላቸው ፤ እንዲሁም በምሳሌነታቸው ሕዝብን ማቅረብ የሚችሉ ሥልጣነ ክህነት ያላቸው ሰዎች ያስፈልጉናል ብለዋል። ጽሕፈት ቤት የሌላቸው አህጉረ ስብከቶች እነማን እንደሆኑ ተጠይቀው ሲመልሱ የበጌምድር ፤ የጐጃምና የኤርትራ አህጉረ ስብከቶች መሆናቸውን አብራርተው እነዚህ አህጉረ ስብከቶች አስተዳደራቸው

www.ethiopianorthodox.org

ከጠቅላይ ቤተ ክህነት የተለየ በመሆኑ እንደሌሎቹ አህጉረ ስብከቶች ይነስም ይብዛም ከቤተ ክህነት በጀት አልተፈቀደላቸውም ። ከዚህም የተነሣ እስከ ዛሬ ድረስ ጽሕፈት ቤት አላቋቋሙም ። ነገር ግን የዳኝነት ሥራ እንደሚሠሩ ተናግረዋል ። በአሁኑ ጊዜ



አቶ፤ ደምሴ ጸጋዬ

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጠ/ ቤተ ክህነት ጽ/ ቤት የሠራተኞች ማስተዳደሪያ ክፍል ጥብቅ ሹም (ፔርሶኔል)

ቤተ ክህነት ለሠራተኞችና ለሥራ ማስኬጃ በዓመት የሚያወጣው ገንዘብ ልክ ምን ያህል ነው?ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ሲመልሱ «ለሠራተኞች ደመወዝ (አንድ ሚሊዮን አራት መቶ ሰባ ዘጠኝ ሺ ሦስት መቶ ሠላሳ ዘጠኝ ብር ። ) ለሥራ ማስኬጃ (ሁለት መቶ ስልሳ አራት ሺ ስድስት መቶ ስድስት ብር)። በጠቅላላው አንድ ሚሊዮን ሰባት መቶ አርባ ሦስት ሺ ዘጠኝ መቶ ሰባ አምስት ብር) ይወጣል» ብለዋል ።

# በስብከት ክፍል ያሉ ንዑሳን ክፍሎች

## የተክሊልና የቅዱስ ቍርባን ክፍል

ስለተክሊልና ቅዱስ ቍርባን ጋብቻ አፈጻጸምና የአሠራር ውል ከክፍሉ ጥብቅ ኃላፊ ከአባ ተፈራ መልሴ የተሰጠው መግለጫ የሚከተለው ነው ።

«ጋብቻ ራሱ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የባረከው የተቀደሰ ሕግ በመሆኑ ቤተ ክርስቲያንም ልጆቿ ምእመናን በተቀደሰ ሕጋዊ መንገድ ጋብቻቸውን እንዲፈጽሙ«ወደኔ የመጣውን ወደ ውጭ አልሰደውም»እያለችና ድምጿን ዘለግ አድርጋ እየጠራች የተለየ ጽ|ቤትና የጋብቻ የክብር መዝገብ አቋቍማ ለብዙዎች ምእመናን ስትፈጽም ቈይታለች ፤ ወደፊትም ትፈጽማለች ።

ቤተ ክርስቲያን ምእመናን ልጆቿ በሥጋቸውም በነፍሳቸውም እንዲጠቀሙ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ትእዛዝ ይፈጽሙ ዘንድ አንድ ወንድ በአንዲት ሴት አንዲት

www.ethiopianorthodox.org



ሴት በአንድ ወንድ ጸንተው ጋብቻቸውን በተክሊልና በቍርባን እንዲያደርጉ ወስናለች በዚህ በተቀደሰ ጋብቻ የተጋቡት ትውልዳቸው የተባረከ ሥራቸው ያማረ ትዳራቸው የተቃና ሆኖላቸው ሰይጣንን ድል ነሥተው የሰላም ኑሮ ይኖራሉ ።

በዚሁ መሠረት ምእመናን ሁሉ ይህንኑ ሕጋዊ መንገድ እንዲከተሉ በድንግልና የሚጋቡትን በተክሊልና በቍርባን ፤ በመአስብነት የሚጋቡትን በንሥሐ ታድሰው ሥጋውን ደሙን ተቀብለው ጋብቻቸውን እንዲፈጽሙ በ፴፮ ዓ፣ ም፣ ተፈቅዶ ሲሠራበት ቈይቷል ።

ተክሊል የማይደገም ሥርዓት በመሆኑ ወንዱ መአስብ ፥ ማለት አግብቶ የፈታ የሆነ እንደሆነ ድንግል የሆነችውን ሴት አገባለሁ ሲል ተክሊሉ ለድንግሊቱ ይፈጸምላታል ፤ ለወንዱ ግን የመአስብ ጸሎት ተደርሶለት ሥጋውን ደሙን እንዲቀበል ይፈቀድለታል እንጂ ሁለተኛ በሚያደርገው ግቢ ሥርዓተ ተክሊል አድርሱልኝ ብሎ ቢጠይቅ ጥያቄውን ለመፈጸም በፍጹም አይቻልም ።



አባ ተፈራ መልሴ

የሥርዓተ ተክሊልና የሥነ ጽሑፍ ምርመራ (ሳንሱር) ኃላፊ

ይህ ሥርዓት ተከብሮ እንዲሠራበት መዝገቡና ፎርሙ ለየሀገረ ስብከቱ ተልኳልና ወደፊት ምእመናን ሁሉ ቤተ ክርስቲያን በምትፈቅደው ሕጋዊ ጋብቻ ጋብቻቸውን እንደሚፈጽሙ ተስፋ እናደርጋለን ።

## የመጻሕፍትና መጽሔቶች ማዘጋጃ ክፍል

የመጻሕፍትና መጽሔቶች ማዘጋጃ ክፍል ሥራና ዓላማ ምን እንደሆነ ከመጻሕፍትና መጽሔቶች አዘጋጅ ከቀሲስ ክንፈ ገብርኤል አልታዬ የተሰጠው መግለጫ የሚከተለው ነው ።

[illegible] ቅጽና በመጽሔት መልክ የሚታተሙ ሥናተ ጽሑፍ ማዘ

ራዊ ኑሮና ሰብአዊ ባሕርይ ከልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያን ቅዱሳት መጻሕፍትና የፍል ስፍና ጽሑፎች እየቀሰመ በዘመናዊ ቋንቋ እያብራራ በመጻፍ መጻሕፍት እያሳተ ለምእመናን ሁሉ በተለይ በትምህርት ቤትላሉ ወጣቶች በወኅኒ ቤት ላሉ እሥረኞች በጦር ሠፈሩ ላሉ ወታደሮች ማስተማሪያና መመከሪያ እያደረገ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወፓትሪያርክ ዘኢትዮጵያ መልካም ፈቃድ እን ዲሁም በብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያ ፓትሪያርክ እንደራሴና የሐረር ሊቀ ጳጳስ ትእዛዝ በነፃ ከማበርከቱም በላይ በዓመት አራት ጊዜ መጽሔቶችንና መግለጫዎችን እያዘጋጀ ያሳትማል ። መጽሔቶቹም የሚታተሙባቸው ፬ቱ ጊዜያት ፤

፩ኛ መስከረም ፲ ቀን ለሚከበረው የተቀጸል ጽጌና የዓፄ መስቀል በዓል ።

፪ኛ ጥር ፲፩ ቀን ለሚከበረው የጌታችን የፈጣሪያችን የኢየሱስ ክርስ ስ ጥም ቀት በዓል ።

፫ኛ በሚያዝያ ወር ለሚከበረው የስቅለትና የትንሣኤ በዓል ።

፬ኛ ሰኔ ፳፩ ቀን ለሚከበረው የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳ ሳት በዓለ ሲመተ ፓትሪያርክ ሲሆን እነዚህን በዓላት ምክንያትና መታሰቢያ በማድ



ቀሲስ ክንፈ ገብርኤል አልታዬ

በድርሰትና ታሪክ ክፍል የመጽሔቶችና የጠይቆ መረጃት ፕሮግራም አዘጋጅ

ረግ የበዓላቱን ታሪክም ሆነ የጊዜውን ዜና መዋዕል ለሕዝብም ትምህርት የሚሆኑ ጽሑፎች አዘጋጅቶ በመጽሔቱ ላይ በማስፈር ሕዝብን ያስተምራል ። ከዚህም ሌላ በየዓመቱ ለሚከበሩ የቅዱሳንና የመላእክት በዓላት ፓንፍሌት እያዘጋጀ በበዓሉ ለተገ ኙት ምእመናን በማደል የበዓሉን ጥንታዊ ታሪክና የአከባበሩን ስነ ሥርዓት ያበሥራል ።

## የራዲዮ ስብከት ክፍል

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በቃል ወይም በመዘዋወር ብቻ የሚሰጠው ትምህርት በቂ አለመሆኑን በማሰብ ከጥቂት ዓመታት

www.ethiopianorthodox.org



ጠን የስብከተ ወንጌል ግዳጇዋን በመፈጸም ላይ ናት ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በራዲዮ ስለምትሰጠው ትምህርት በሰፊው ያብራሩ ልን ዘንድ በመንበረ ፓትሪያርኩ ስብከትና ድርሰት ክፍል የራዲዮ ፕሮግራም ኃላፊ የሆኑት ርእሰ ደብር ጥዑመ ልሳን ካሣሁንን ጠይቀናቸው የሚከተለውን መልስ ሰጥተውናል ።



ርእሰ ደብር ጥዑመ ልሳን ካሣሁን

በታሪክ ድርሰትና ስብከት ክፍል የሬዲዮ ስብከተ ወንጌል ኃላፊ

፩ኛ/ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እስከ ፶፬ና ፶፭ ዓ. ም. ድረስ በራዲዮ አትሰብክም ነበር ግን ከተባሉት ዓመታት ጀምሮ በየዕለቱ በሬዲዮ መስበኳ ይታወቃል ። ይህንን የሬዲዮ ስብከት እንድታደርግ ያነሣሣት ምንድነው ?

<u>መልስ</u> የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እንደዛሬው አዘውትራ በሬዲዮ አትስበክ እንጂ ከ፶፬ም ሆነ ከ፶፭ ዓ፣ ም፣ በፊት በነበሩ ዘመናት በየሳምንቱ እሑድ እሑድና በዓበ ይት በዓላት ጊዜ ከሊቃውንቱ እየተመረጡ ይሰብኩ እንደነበር እሙን ነው ። በዚህ አኳኋን ትምህርቱ ቀስበቀስ ተጀምሮ ሲሰጥ ከቈየ በኋላ በቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ሥር ይካሄድ በነበረው የመምህራን ኮርስ ገብተው ለሦስት ዓመት የተመደበላቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ጊዜው የሚፈቅደውን የዘመኑን ትምህርት አጠናቀው በ፶፬ ዓ፣ ም፣ የወጡት ፴፮ መምህራን በቤተ ክህነቱ በኩል በስብከተ ወንጌል ሥራ ተቀ ጥረው በየጠቅላይ ግዛቱ እንዲሠሩ ተደርጎ ስለ ነበር በሸዋ ጠቅላይ ግዛት ከተላ ኩት ሰባክያን ጥቂቶቹ በ፶፭ ዓም ወደ ዋናው መሥሪያ ቤት ተዛውረው ዘወትር ጧት በኢትዮጵያ ሬዲዮ ጣቢያ የሃይማኖትና የግብረ ገብ የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓትና ባህል የመሳሰሉትን ሁሉ ለሕዝቡ በሚገባው መንገድ እያብራሩ እንዲያስተምሩ ተደረገ ። ይህንን ለማድረግ ቤተ ክርስቲያንን ያነሣሣት ዋናው ምክንያት መድኃኒታ ችን ኢየሱስ ክርስቶስወአንጌል ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ ብሎ ባዘዘው መሠረት ቃሉን ለማዳረስና ትእዛዙንም ለመፈጸም ነው ከዚህም በስተቀር በእግር ተዘዋውሮ ከሚደ ረገው ስብከት ይልቅ በሬዲዮ የሚተላለፈው ትምህርት ለሁሉም በቶሎ የሚደርስ መ ዘወትር ጧት በኢትዮጵያ ሬዲዮ ጣቢያ አማካይነት የሚ

www.ethiopianorthodox.org

ተላለፈውን ትምህርት ከኢትዮጵያ አልፎ ለሌሎችም አህጉራት የሚደርስ መሆኑን ከየአህጉራቱ የሚጸፍልን የምስጋና ደብዳቤና የሚቀርብልንም አስተያየት ሊያስረዳን ችሏል ።



አቶ ብርሃኑ ገብረ አማኑኤል

የታሪክ ድርሰትና ስብከት ክፍል ዋና ጸሐፊ

፱ኛ በሬዲዮ የሚሰጠው የጥቂቶች ሊቃውንት ድምፅ ብቻ ነው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ሊቃውንት ሲኖሩዋት ለምን አይሰብኩም ?

መልስ ርግጥ እንደተባለው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብዙ ሊቃውንት ያሏት መሆኑ አይካድም ነገር ግን ያሉት ሁሉ በሬዲዮ ይስበኩ የተባለ እንደሆን ከከተማው ወጣ ብለው የሚገኙትና ሬዲዮም የሌላቸው ሁሉ ትምህርቱ ሳይደርሳቸው ቢቀር በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት እንደዚያ ሰነፍ አገልጋይ ያለ ወቀሳ የሚያስከትል በመሆኑ ጥቂቶቹ በሬዲዮ እንዲሰብኩ ሲደረግ ብዙዎቹ ግን ወደየጠቅላይ ግዛቱ ተልከው እንዲያስተምሩ በመደረጉ ነው የጥቂቶቹ ሊቃውንት ድምፅ ሊሰማ የቻለው ።

፲ኛ የሬዲዮው ስብከት ሃይማኖትን ብቻ ሳይሆን የሰዎችን ጠባይ የሚያንጽና የማኅበራዊ ኑሮ ድጋፍ የሆነ ትምህርት ይሰጥበታል ይህ ሲሆን ለምን ሰፋ ብሎ ጧትና ማታ እንደ ሁዳዴው ጊዜ አይሰጠውም ?

መምህራኑስ በዓቢይ ጾም እንደሚደረገው ለምን በብዛት ተራ ገብተው አይሰብኩም?

መልስ ይህ ዓይነቱ ጥያቄ ብዙ ጊዜ ደርሶናል ምን ጊዜም ቢሆን ይህ የስብከተ ወንጌል ሥራው ሕዝብን ማገልገልና የሚቀርበውንም አስተያየት ሆነ ጥያቄ ተቀብሎ በሥራ ላይ ማዋል ዋና ዓላማው እንደ...

www.ethiopianorthodox.org



እንዲሰጥ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የማስታወቂያ ሚኒስቴር ጥያቄውን እንደ ሚቀበለው እምነት ተጥሎበታል ።



አቶ ገብረ ሚካኤል ብሩ

የዜና ቤተ ክርስቲያን ጋዜጠኛና
የተስፋ ሕይወት ፕሮግራም አዘጋጅ

፲፩ኛ መምህራኑስ በዓቢይ ጾም እንደ ሚደረገው ለምን ተራ ገብተው አይሰብኩም? ስለተባለው ጥያቄ በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙት የደብር አስተዳዳሪዎች አንዱ የታዕካ ነገሥት በአታ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ክቡር ሊቀ ሊቃውንት ኃይለ መስቀል ገብረ መድኅን የሥራው ተካፋይ ሆነው በመሥራት ላይ ይገኛሉ ሌሎችም የደብር አስተዳዳሪዎች የማታው ክፍለ ጊዜ ከማስታወቂያ ሚኒስቴር ሲፈቀድልን የሥራው ተባባሪዎች እንደሚሆኑ ተስፋ እናደርጋለን ።

፲፪ኛ በስብከቱ ፕሮግራም በኩል ከማስታወቂያ ሚኒስቴር ሠራተኞች ጋር ያለው መግባባት እንዴት ነው ?

መልስ በዚሕ አጋጣሚ ጊዜ በማስታወቂያ ሚኒስቴር ሠራተኞችና በስብከቱ ፕሮግራም በኩል ስላለው የሥራ መግባባት እንድገልጥ በመጠየቄ በጣም ደስ ይለኛል ምን ጊዜም ቢሆን በዚህ ባለንበት ዓለም ላይ ማንኛውም ሥራ ሊከናወን የሚችለው በሠራተኞችና በአሠሪዎች መካከል የመግባባት መንፈስ ያለ እንደሆነ ነው ። በዚህ መሠረት እኔ ይህንን የሬዲዮ ፕሮግራም በኃላፊነት ይገዥ እንድሠራ ከተደረገበት ዘመን ጀምሮ አሁን እስካለንበት ጊዜ ድረስ በባለሥልጣኖቹ ዘንድም ሆነ በቴክኒሺያኖቹ በኩል ያለው የአሳብ ድጋፍና ጥሩ ጠባይ እንዳየሁትና እንደተመለከትኩት ለፕሮግራማችን ታላቅ ኃይል ለእኛ ለሠራተኞቹ የመንፈስ ደስታ ሆኖ አግኝቼዋለሁ ምክንያቱም በየጊዜው ከሚያደርጉልንና ከሚፈጽሙልን ርዳታዎች ብዙዎቹን ትቼ አንዱን ስጠቅስ በአንዳንድ ችግር ምክንያት ሰዓት አሳልፊን ስንደርስ የተወሰነውን ሰዓት አሳልፋችኋልና በታ የለም በማለት ሳየጕላሉን በቅንነት መንፈስ ሥራውን ሠርተው የማበረታቻ ምክራቸውን ስለሚለግሱን ነው ። በጠቅላላው ስለስብከቱ ፕሮግራም ከእኛ ይልቅ በይበልጥ እነሱ ያስቡበታል ብል አላተሳሳትኩም ።

፭ኛ ስለሬዲዮ ስብከት ከሕዝብ የሚቀርብ ነቀፋ ወይም ምስጋና እንዳለ ቢያ ብራሩልን

መልስ ምን ጊዜም ቢሆን አንድ ሥራ ሲሠራ ነቀፋም ሆነ ምስጋና አይቀርለትም ምክንያቱም የሥራውን አድካሚነት ያላወቁ ሲነቅፉ የሥራውን አስቸጋሪነት ያወቁና የተረዱ ደግሞ ምስጋና ከመሥጠትም አልፈው የማበረታቻ ድምፃቸውን የሚሰጡ አሉ የሆነ ሆኖ በሁለቱም በኩል የቀረበውን ሃሳብ እንዳመዛዘነው ከነቃፊዎቹ የአመስጋ ኞቹ ድምፅ የሚበልጥ መሆኑን በየጊዜው በሚደርሰን ጽሑፍ ለማወቅ ችለናል ።



አለቃ ብርሃኑ መኰንን

የስብከት ወንጌል ፕሮግራም አባል

# የወጣቶች አንድነት ማዕከላዊ ጽ| ቤት

በብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ የኢትዮጵያ ፓትረያርክ እንደራሴና የሐረር ጠ/ ግዛት ሊቀ ጳጳስ መልካም ፈቃድና ትእዛዝ በመንበረ ፓትረያርኩ የወጣቶች አንድ ነት ማዕከላዊ ጽ ቤት ተቋቁሞ ሥራውን ማካሄድ ከጀመረ እነሆ ሰባት ወር ሆኖታል፤ የጽ| ቤቱም ዓላማ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሃይማኖት ያሉ ወጣቶች መንፈሳዊ ይዘታ ቸውን ለማጠንከር በየአብያተ ክርስቲያናትና በየት| ቤቱ መንፈሳዊ ማኅበር የቋቋሙ ትና በማቋቋም ላይም የሚገኙት ሁሉ የአንዲት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ



ክርስቲያን ልጆች እንደ መሆናቸው መጠን በአንድ ደንብና ሥርዓት ተጠቃለው እንዲ ማሩና አንድነታቸውን ለማጠንከር ርስ በርሳቸውም ለመወያየት እንዲችሉና፤የአባቶችን ዓላማ ተከትለው ለወደፊቱ ፍጹማን እውነተኞች አባቶች እንዲሆኑ ለማብቃት ከመ ሆኑም ሌላ ከዓለም አብያተ ክርስቲያናት ወጣቶች ጋር የጠበቀ ግንኙነት አድርገው በየ ጊዜው በሚደረገው የዓለም ወጣቶች መንፈሳዊ ስብሰበ ላይ እየተገኙ ሀሳብ ለሀሳብ



አቶ ጥበቡ ተገኝ

የወጣቶች አንድነት ማዕከላዊ ጽ/ ቤት ዋና ጸሐፊ ።

ለመለዋወጥና የራሳቸውን አእምሮ ለማጐልመስ ፥ የቤተ ክርስቲያናቸውንም እድገት ከፍ ለማድረግ እንዲችሉ በማሰብ ሲሆን እስከ አሁንም ድረስ በዚህ ጽ| ቤት በዓባልነት የተመዘገቡት ማኅበሮች ፴፫ ደርሰዋል » ሲሉ የማዕከላዊው ጽ| ቤት ዋና ጸሐፊ አቶ ጥበቡ ተገኝ ገለጡ ።

ከ፵፫ኛው ገጽ የዞረ

| ተራ ቁ | የመሬቱ መደብ | የመሬቱ ልክ ጋሻ | ማ | ሚ |
|---|---|---|---|---|
| ፩ | ለም | ፩ሺ፰፻፴ | ፳፬ | ፵፲ |
| ፪ | ለም ጠፍ | ፮ሺ፪፻፷፰ | ፶ | ፶፰ |
| ፫ | ጠፍ | ፯ሺ፸፻፶፪ | ፳፩ | ፳፪ |
| | ድምር | ፳፱ሺ፻፵፬ | ፺፬ | ፳፫ |
| | ቁጥርገባርናየርስትአገር፤ | ፴፫ሺ፮፻፯ | — | — |

| | የገንዘቡ ልክ አሥራት ብር | ሣ | ት/ታክስ ብር | ሣ |
|---|---|---|---|---|
| | ፮፻፹፫ሺ፩፻፹፩ | ፵፫ | ፫፻፴ሺ፩፻፹፱ | ፵፰ |
| | ፪፻፯ሺ፶፯ | ፲፯ | ፩፻፲፯ሺ፩፻፹፰ | ፶፱ |
| የትግሬ ወደቅ | ፫፻፲፰ሺ፶፩ | ፹፫ | ፩፻፲፰ሺ፪፻፹፯ | ፳፫ |
| | ፱ሺ፩፻፹፰ | ፳ | ፫ሺ፱፻፶፯ | ፳ |
| የወሎ ›› | ፩ሚሊ፫፻፲ሺ፰፻፵፯ | ፳፫ | ፳፻፰፲ሺ፱፻፲፪ | ፹፯ |
| ጠቅላላ ድምር | ፪ሚሊዮን፩፻፹፱ሺ፯፻፰ | | | ፶ ነው |

፪ኛ ለየገዳማቱና ለየአድባራቱ ለየገጠሩ ቤተ ክርስቲያን ስለተሰጠው መሬት ልዩ

www.ethiopianorthodox.org

ነት እንዳለው ለተባለው ርስት የተሰጠው ለቤተ ክርስቲያኑ ቢሆንም የሚጠቀሙበት አገልጋዮችና መነኰሳት ስለሆኑ ልዩነት የለውም ።

፫ኛ ለቤተ ክርስቲያን የተሰጠው ርስት ጕልት ለተባለው መሬቱ በየቤተ መቅደስ ተሞልቶ ከላይ ከተመለከተው ድምር ላይ ይገኛል ።

፬ኛ ስለቤተ ክህነት መሬት ምን ችግር እንዳለ ለተባለው ፤ የመገመቻው ክርኔና ሠራተኛው የገንዘብ ሚኒስቴር ስለሆነ አንዱ ተጕራጅ ለባለርስቱ ሲሰጥ ለአውራጃ ውና ለሀገረ ስብከቱ እንዲሁም ለዋናው መሥሪያ ቤት የግምቱ ማስረጃ ባለመሰጠቱ ከፍ ያለ ችግር አስከትሏል ።

፭ኛ ችግሩ በምን ዓይነት እንደሚቃለል ለተባለው ፤

(ሀ) የ፺፭ ዓ ም መገመቻ ክርኔ ሁለተኛውን ተጕራጅ ለየሀገረ ስብከቱ እንዲሰጥ

(ለ) ለወደፊቱ የመገመቻው ክርኔና ሠራተኛው የቤተ ክህነት እንዲሆን ቢደረግ ለሥራው አፈጻጸም በጣም ቀና ይሆናል ።

---

ከ፵፫ኛው ገጽ የዞረ

<u>መልስ</u> ከጐጃም ፤ ከጐንደር ፤ ከአሥመራ በቀር በአዲስ አበባና በሌሎችም ሀገረ ስብከቶች በቀለብ ለሚተዳደሩ ።

ሀ፣ ክህናት

ለ፣ ሰባክያን

ሐ፣ መምህራን

መ፣ ሠራተኞች

ደመወዝ ከቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ቦርድ ለዓመት $ 1.473.369 (አንድ ሚሊዮን አራት መቶ ሰብዓ ሦስት ሽህ ሦስት መቶ ስድሳ ዘጠኝ የኢ.ት/ ብርና ፤ በሥራ ማስኬጃም በኩል እንደዚሁ በ፭ኛው ተራ ቍጥር ከተገለጹት ጠብላይ ግዛቶች በቀር ለዓመት $ 264.606 (ሁለት መቶ ስድሳ አራት ሽህ ስድስት መቶ ስድስት ብር) በድምሩ ፤ $ 1.737.975 (አንድ ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰላሳ ሰባት ሽህ ዘጠኝ መቶ ሰብዓ አምስት ብር) በተፈቀደው በጀት መሠረት ነው ።

<u>ጥ ያ ቄ</u> ፫ኛ በአዲስ አበባና በሀገረ ስብከቱ ለደመወዝና ለሥራ ማስኬጃ የሚደረገው ወጭ ከመሬት ግብርና የት/ ታክስ ገቢ ነው? ወይንስ ከቤት ኪራይ ?

<u>መልስ</u> በአዲስ አበባም ሆነ በሀገረ ስብከቱ ለደመወዝና ለሥራ ማስኬጃ የሚደረገው ወጭ አንደኛው ተራ ቍጥር ከተገለጹት የገቢ አርእስቶች ስም በሚገኘው ገቢ ነው ።

<u>ጥ ያ ቄ</u> ፬ኛ ደመወዝ በወቅቱ አይከፈልም ይባላል ምክንያቱ ምንድን ነው ?

<u>መልስ</u> የደመወዙ አከፋፈል እንደተባለው ሳይሆን እንደ ሌሎቹ መ፣ ቤቶች ሁሉ በየወሩ መጨረሻ ይከፈላል ።

<u>ጥ ያ ቄ</u> ፭ኛ በበጀት አወሳሰን በኩል በሸዋና በሌሎቹ አጉሀረ ስብከቶች ልዩነት አለው ይባላል ርግጥ ነው ?



<u>መልስ</u> የሸዋንም ሆነ የሌሎችን ሀገረ ስብከቶች በጀት ገቢና ወጪአቸውን በጠቅላላው እያዘጋጀ ከአስተያየት ጋር ለቦርድ በማቅረብ የሚያስወስነው የቤተ ክህነት ጠቅላይ ጽ፣ ቤት እንደመሆኑ መጠን በዚህ ሁኔታ እንደ አቀራረቡና እንደ ክፍለ ሀገሩ የደመወዙም ሆነ የሥራ ማስኬጃው ልዩነት ሊኖረው ይችላል ።


<u>ጥ ያ ቄ</u> ፮ኛ የሸዋና የቀሩት አህጉረ ስብከቶች ደመወዝ ሥራ ማስኬጃ የገንዘብ ወጭ አከፋፈል ከአዲስ አበባ ጠቅላይ ግምጃ ቤት ነው ? ወይስ በያሉበት ?

<u>መልስ</u> የሸዋ ሀገረ ስብከት በ፮ኛው ተራ ቍጥር እንደገለጽኩት ሁሉ ከአስወሳኙ መ፣ ቤት ተወስኖ በተላለፈለት በጀት መሠረት የጽሕፈት ቤቱንና በመናገሻም አውራጃ የሚገኙትን ወረዳዎች ደመወዝና ሥራ ማስኬጃ ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ግምጃ ቤት እንዲከፈለው በመጠየቅ ገንዘቡን በድምር እየተረከበ በዝርዝር ሲያከፋፍል ። የቀሩትን አውራጃዎች ግን ለደመወዝም ሆነ ለሥራ ማስኬጃ ከሀገረ ስብከቱ የተላለፈላቸውን ወጪ በመጠበቅ ከገቢያቸው በኃላፊነት ወጪ ያደርጋሉ ።

<u>ጥ ያ ቄ</u> ፯ኛ ቤተ ክህነት በየዓመቱ ከአዲስ አበባና ከየሀገረ ስብከቱ ከሚያገኘው ገቢ ከፍተኛ ግምት ያለው በየትኛው የገቢ ምንጭ ላይ ይመስልዎታል ?

<u>መልስ</u> በአንደኛው ተራ ቍጥር የገለጽኩት የገቢ ሂሳብ እንደሚያስረዳው ከአሥራት ክፍል የተገኘው መሆኑን ከማስረዳቱም በላይ ሊገኝም በሚገባው ግምት የአሥራቱን ገቢ ከፍተኛነት ማረጋገጥ ተችሏል ።

---



[illegible] ፡ ይዜምሩ እንዘ ይብሉ ሃሌ ሉያ ።

www.ethiopianorthodox.org

# ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት መንፈሳዊ ተግባር


# ሥዕላዊ መግለጫ



ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት በሲኖዶስ የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት ሲሠሩ




ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ስለ ዓለም ሰላም ሲጸልዩ ።





ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ በደብረ ሊና የስብከተ ወንጌል ድርጅት ሲያቋቁሙ

www.ethiopianorthodox.org



ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ በናዝሬት የስብከተ ወንጌል ድርጅት ሲያቋቁሙ



ብፁዕ አቡነ ቴዎፍሎስ በሀ.ይ የተቋቋመውን የቀሳውስት ማሠልጠኛ ት| ቤት መርቀው ሲከፍቱ፡

ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
D.N Solomon Yohannes
0911850113
0111/271609

www.ethiopianorthodox.org